# ይህን ታምኛለሽን?

ከመጸለያችን በፊት፡ እንዲህ ማለት እፈልጋለሁ፡ ትናንት ማታ፡ ይመስለኛል፡ አንዲት እመቤት፡- “እንደምንልሽ ካደረግሽ፡ የጭንቅላት እብጠት ያለው ህጻን... እብጠቱ ይቀንሳል” ብያት ነበር። ከዚያ በኋላ ትናንት ማታ፡ የህጻኑ ጭንቅላት ቀነሰ፡ እብጠቱ በአንድ ክር መለኪያ ግማሽ-ኢንች ያህል ቀንሷል። እመቤቲቱ ይዛው መጥታለች።

2 ስለዚህ፡ እህቴ፡ እንደዚያ ያደረግኩት፡ በምክንያት ነው። አየሽ? ተጨባጭ ነገር ሲሆን ካየሽ፡ እምነትሽ እንዲቀጥል፡ እና እምነትሽም እንዲጨምር ያደርገዋል። አንዳንዴ ሰዎችን፡ እንዲህ አደርጋቸዋለሁ፡ ሰውየው እንዲነሳ እጠይቀውና፡ ምናልባት፡ አንድ ሁለቴ ተንቀሳቅሰ፣ እጅን አወዛውዝ፣ ጣትህን አንቀሳቅስ እለዋለሁ፡ ነገር ሁሉ መልካም እንደሆነ እንዲያዩ ስለምፈልጋቸው፡ ማድረግ የሚችሉትን ነገር እንዲያደርጉ እጠይቃቸዋለሁ። እነርሱ ግን አይሆንም ብለው ስለሚያስቡ ይጨነቃሉ፡ ነገር ግን ሁሌም ይሆናል። አያችሁ? መሆኑም ግድ ነው።

3 አሁን እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ፡ ስንቶች ናችሁ? ራሶቻችንን ዝቅ አድርጉና። እጆቻችሁን አንስታችሁ፡ “ጌታ ሆይ፡ አሰበኝ” በሉት?

4 ጌታ ሆይ፡ በውድ ወዳጄ፡ በፖል ራደር፡ የተዘመረ ታላቅ የቤተክርስቲያን መዝሙር፡ “እመን ብቻ” ስንሰማ፡ በአባቱ ተይዞ ወደ ደቀ መዛሙርት የመጣውን ልጅ፡ ትዝ ይለናል፡ ኢየሱስ አጋንንትን እንዲያወጡ እና ድውያንን እንዲፈውሱ ሥልጣን ከሰጣቸው ከአሥር ቀን በኋላ፡ ወድያው የሚጥል በሽታ ባለበት ሙሉ በሙሉ ተሸነፉ። ጌታ ሲመጣ አይተው። አባትየው ሮጦ፡ “ጌታ ሆይ፡ ማረኝ። ልጄ በዲያብሎስ እጅግ ተሠቃየ። ደቀ መዛሙርትህ እንዲፈውሱት አመጣሁት ሊፈውሱት አልቻሉም።”

5 ኢየሱስም “እመን ብቻ። ካመንክ፡ እኔ እፈውሰዋለሁ፡” አለው። አምላክ ሆይ፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለአፍታም አልተለወጥክም፣ አንተ አፍቃሪ፣ ጣፋጭ እና አዛኝ አምላክ ነህ። እንደ ጥንቱ፡ ዛሬም ያው ነህ። ጌታ ሆይ፣ እንደዚያ አባት፣ የኛም ጩኸት “ጌታ ሆይ አለማመናችንን እርዳ” ነው። አባት ሆይ፤ እጅግ ቀላል ነው፡ እኛ ግን በዚህ ተሰናክለናል።

6 ትናንት ማታ ህጻኑን ስለዳሰስከው ምስጋና እና ክብር እናቀርባለን። ያበጠውን ቅል፡ አይተን፡ ከውስጥ ተገፍቶ የወጣ አጥንት፡ ትናንት ማታ ግን ግማሽ ኢንች ያህል ቀንሶ አይተናል። አባት ሆይ፡ ምስጋናችን ብዙ ነው። ዶክተሮቻችን ለችግሩ የሚሆን መፍትሄ የለም፡ ማድረግ የሚቻላቸው አንዳች ነገር የለም፡ አንተ ግን አሁንም አምላክ ነህ፡ የሁኔታዎች ሁሉ ጌታ ነህ። አባት ሆይ፡ ስለዚህ እናት እናመሰግንሃለን። ስለ ታማኝነቷ፣ ስለ መልካምነቷ፣ ክሩን አምጥታ በዚህ ትንሽ ወረቀት ላይ ለመለጠፍ ስለመታዘዝዋ፡ ስለ እግዚአብሄር ክብር ለምስክርነት በህዝቡ ፊት ማሳየቷ እናመሰግንሃለን። ልጇም ጤነኛ ሆኖ፡ ስለ አንተ ክብር፡ በህይወት ይኑር።

7 አባት ሆይ፡ የተነሱ እጆች ሁሉ ተመልከት። ሁሉም ጥያቄ አላቸው። አባት ሆይ፡ እኔም፡ እንስቻለሁ፡ ልመና አለኝና። ሌሎች ልመና ያላቸው ብዙ ሰዎችም፡ ልመናቸውን፡ በዚህ ሳጥን ውስጥ፡ በደብዳቤ አስቀምጠዋል። ጌታ ሆይ፡ እንዲሁ ይሁንላቸው፡ ዛሬ ማታ ሁሉም መልሳቸውን ይቀበሉ። የዚህች እናት ምስክርነት ወስደው፡ አንተ ያልከው ነገር ሁሉ እንደሚሆን ለማየት እንደ ምሳሌ ይቀበሉት። ከአንተ... ነውና... ያለቀለት ስራ ነው። እኛም የሚጠበቅብን ተቀብለን ተግባራዊ ማድረግ ብቻ ነው።

8 ጌታ ሆይ፡ እነዚህ ደብዳቤዎችን እና መሃረቦችን፡ አስባቸው፣ ያስቀመጧቸው ሰዎች ሁሉ፡ የተፈወሱ ይሁኑ። አባት ሆይ፡ እጆቻቸውን ያነሱ ሁሉ፡ የልባቸውን መሻት ያግኙ። በኢየሱስ ስም ጸለይን። አሜን። አረፍ አረፍ በሉ።

9 የሴቲቱ ክር፡ ላሳያችሁ ፈልጌአለሁ (ይሄ ነው። አህ-ሀህም።)... ጌታ በመንፈስ ቅዱስ ትናንት ማታ ቃል እንደገባልን የሕፃኑ ጭንቅላት ቀንሷል። አይደደንቅም ወይ? ስለዚህ፡ እምነት እንዲኖረን እና እንድናምን ብዙ ድፍረት ይሰጠናል።

10 እንደው፡ በማርቆስ 11:23፣ ላይ ኢየሱስ ዛፏን፦ “ከዛሬ ጀምሮ ማንም ከአንቺ አይብላ፡” ሲላት አልጮኸም ይሆናል። እውነት ለመናገር፡ ከደቀ መዛሙርት፡ አንዱ ብቻ እስኪሰማ... ሳያካብድ፡ እጅግ ቀለል አርጎ ተናገራት። የሚጥል በሽታ... የነበረበት ወጣት፡ በኢየሱስ ፊት በቀረቡት ጊዜ፡ አሰቦት የማያውቅ ከባድ ተፋላሚ ገጠመው፡ እንደሞተ ሰው ሆኖ፡ ምድር ላይ ወደቀ፡ ከሐዋርያት ይልቅ የላቀ እምነት ያለው ሰው እንደተጋፈጠው ግን አስተውለዋል።

11 በመለኮታዊ ፈውስ የማያምን አንድ ሰው፡ አሁን ይህ እንዲያስተውል እፈልጋለሁ። ኢየሱስ መናፍስትን እንዲያወጡ ኃይል ሰጥቷቸው ነበር፣ ግን አልቻሉም። ያልቻለው ኃይሉ አይደለም፡ ያልቻሉት እነርሱ ናቸው። ኢየሱስ ነግሯቸዋል፡

“እኛ ልናወጣው ያልቻልነው ለምንድነው? ”

“በአለማመናችሁ ምክንያት፡” አላቸው።

12 ዛሬም ቤተ ክርስትያን ኃይሉ አላት። እግዚአብሄር ኃይሉን ከቤተ ክርስትያን ፈጽሞ አላነሳም፡ ቤተ ክርስትያን ግን በተግባር ለማሳየት በቂ እምነት የላትም። በቀላሉ። ይሄው ነው። አንዳንዴ ማወሳሰብ እንሞክራለን፣ ወንጌልን ቀለል ባደረጋችሁት መጠን ግን፣ የበለጠ እውነታ ታዩበታላችሁ፣ ቀለል ካደረጋችሁት፡ እግዚአብሄር ከተናገረ፡ ሆነ ነው፡ በቃ። እመንና፡ ቀጥል።

13 ኢየሱስ ዛፏን “ሰው ከአንቺ አይብላ” ባላት ጊዜ፡ ቅጠሎቿ እንደ ድሮ፡ ቆንጆ እና ደማቅ ነበሩ። ቅርፊቷም ጥሩ ነበር፡ በስሮቹ መካከል በመሬት ውስጥ ግን፡ ህይወቷ መወለጋገድ ጀመረ።

14 ስለዚህ በካንሠር ይሁን፡ በምታስቡት በየትኛውም አይነት በሽታ ሁሉ—እንዲሁ ነው። የእግዚአብሄር ቃል በምትቀበሉበት ጊዜ፡ ካንሠሩ፡ ምናልባት ስር ውስጥ የዘለቀ፡ እጃችሁም እንደ ደረቀ ቢሆንም። “ማመን ከቻላችሁ።” እና

ጥግ ላይ መሰራቱ የማይቀር ነው። አያችሁ? ይህ ግን፡ ከመለኰታዊ ፈውስ ጋር አይገናኝም።

15 ኢየሱስም፡ "በልባችሁ ሳትጠራጠሩ፡ ያላችሁት እንደሚፈጸም እምናችሁ፡ አንተ ተራራ 'ከዚህ ተነሣ፡' ብትሉት ግን፡ ያላችሁት ይሆንላችኋል ብሏል።" ደስ አይልምን? ያ ከማን መጣ? ሰማይ እና ምድር ቢያልፉ፣ ቃሉ... ቃሉ ግን፡ ፈጽሞ ከማያልፍ... ከእግዚአብሄር ልጅ መጣ።

16 ይሄን ማድረግ የምትችሉበት ብቸኛው መንገድ፣ ትክክለኛው ዓላማ፡ እና ትክክለኛ ተነሳሽነት ሲኖራችሁ ብቻ ነው። አሁን፡ ወዲህ ውጥቼ፦ "ይሄን ተራራ አንቀሳቅሼ አሳያችኋለሁ በማለት፡ 'አንተ ተራራ፡ ተነሣ ብለው።'" በፍጹም አይነሣም። በጭራሽ። ምንም ቢኖረኝም አይነሳም። ከሁሉ በፊት... የእግዚአብሄርን ፈቃድ ማወቅ አለባችሁ።

17 ብዙ ጊዜ፡ በፀሎት ሰልፍ ላይ––በጣም የምቸገርበት፡ ምክንያት ይህ ነው፡ በሰልፉ እና በመሳሰለው ውስጥ የሚመላለስ ነገር ሰላለ ነው፡ ዳግም የሚመጣበት ቦታም ይህ ነው። አያችሁ፡ ንሰሓ ያልተጋባ ሐጢያት ካለባችሁ... ክፉ መንፈስ ከመገሰጼ በፊት፡ እኔን አስተውላችሁኛል? ይህ እንዳይፈጸም የሚከለክል ነገር እንዳይኖር እርግጠኛ እስክሆን ድረሰ ህይወታቸውን በደንብ አጤነዋለሁ፡ አያችሁ፡ ምክንያቱ፡ በጸጋ ሰጦታዎች፡ ችግር ውስጥ መውደቅ እንደምትችሉ እንዳትረሱ።

18 እግዚአብሄር፡ ሙሴ፡ የተባለውን ሰው ነብዪ አርጎ ሲሾመው... ታስታውሳላችሁ፡ ውረድና፡ አለቱን ተናገር አለው። ነብዪውም እጅግ ተነቃቃና፡ ወጥቶ፡ ዓለቱን መታው፡ ሰለ ክርሰቶስ መከራ ሲያመላክት፡ ዳግም እንደሚሞት ወይም እንደሚመታ ያመላክት ነበርና። ማመንጨት ችሏል፡ የእግዚአብሄር ፈቃድ ግን አልነበረም።

19 ኤልሳዕ ወጥቶ ያደረገው ነገር የእግዚአብሄር ፈቃድ አለበት ብየ አላምንም፡ ህጻናት ወጥተው ሰለ መላጣነቱ ባፌዙበት ጊዜ፡ ያን ማድረግ ነበረበት ብየ አላምንም። እሱ ግን ተበሳጨና፡ ነብዪ ሰለነበረ፡ ህጻናቱን ረገማቸው ሁለት ሴት ድቦች ወጥተው ከመካከላቸው አርባ-ሁለት ንጹሃን ህጻናት ገደሉ። አያችሁ? እኔ ያንን ማድረግ ነበረበት ብየ አላምንም። እና–– በቃ... እኛም...

20 ጌታ፡ በቤተ ክርሰትያን ኃይል ከመሰጠቱ በፊት፡ ምን ሊያደርግ እንደሚችል ቤተ ክርሰትያን እንድትረዳ፡ ይፈልጋታል እላለሁ።

21 ምናልባት... እግዚአብሄር ፈቅዶ፡ ቀጣይ ጊዜ ከመጣሁ፡ እንዲህ የመሳሰሉ ነገሮች ለመማር፡ ጊዜ ይኖረናል፡ ሊፈጸሙ የተዘጋጁ ነገሮችን እናያለን፡ ያኔ አብዝተን እንረዳዋለን።

22 ቃል ሰትናገሩ ግን፡ ሳትጠራጠሩ፡ ከውስጥ ከልባችሁ፡ "ጌታ ሆይ፡ አምናለሁ፡" በሉ...

23 ለምሳሌ፡ እኔ በአንድ ሸለቆ ነኝ እንበል፡ እናም... ለሚልዮኖች ሰዎችን፡ እየሰበኩ ነኝ፡ ከተራራው ወዲያ ማዶ ግን፡ ክርሰቶስን ሳያውቁ ሊሞቱ ያሉ፡ አንድ መቶ የሚያህሉ ሰዎች አሉ። መቼም፡ የምሰብካቸው አንድ ሚልዮን አሉ፡ የሆነ ነገር ግን፡ በልቤ ውስጥ እንዲህ ይለኛል፦ "ወደነዚያ ሰዎች

ተሻገር። ቅረባቸው።እየጠፉ ነው።" በግሌ መሄድ አልፈልግም፡ በውስጤ ግን አንድ ነገር አለ። አያችሁ፡ እግዚአብሄር ሲሰራ ማለት፡ እንዲህ ነው። ወደዚያ የመሄዱ ዓላማ፡ እና ተነሳሽነቱን ምን እንደሆነ አስተውሉ፡ ለግል ጥቅም አይደለም... አሁን ግን፡ እኔ "በጣም ጥሩ... " ብየ፡ ወደዚያ የምሄድበት ዓላማው ልክ ሆኖ፡ ወደ ስፍራው ከደስኩ በኋላ ግን ትልቁ ተራራ አይቼ፡ እንዲህ ባስብ፡- "ታውቃለህ፡ ወደዚያ ተራራ ልውጣና እነዚያን መቶ ሰዎች ላድናቸው፡ ሰዎቹም አንድ ቀን፡ ታላቁ ሚሽነሪ ወንድም ብራንሃም፡ ብለው ሐውልት ያቆሙልኛል ብል።" ተነሳሽነቴ፡ የተሳሳተ ሆኗል። ስለዚህ ተራራው አይወድቅም። አይንቀሳቀስም፡ ጌታዬ።

24 እግዚአብሄርም በልቤ ውስጥ እየመራኝ፡ ተነሳሽነቴ እና ዓላማየ ትክክል ሲሆን ግን፡ ወደ ተራራው ራስ፣ በተራራው ዙርያ፣ ወይም በተራራው ስር ባልደርስም'ኳ፡ "አንተ ተራራ፡ ተነቀል፡" ብለው። ምናልባት... በትክክለኛ መንፈስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቼ፡ እንደ ጌታ ፈቃድ፡ እኔ ይህን ስናገር፡ አንዲት ማንኪያ የምታክል አፈር እንኳን ሳያስቀር፡ ጉዞውን ያስጀምረዋል። በቀጣይ ቀን ሁለት ፓውንድ ያፈርሰዋል። ቀጣይ ቀን የቶን ሩብ። በአንድ ወር ውስጥ፡ ምናልባት አምስት ቶን ያህል አይኖርም። ምን ገጠመው? ላይታያችሁ ይችላል፡ ይሁን እንጂ፡ መፍረስ ጀመሯል። እኔም እግዚአብሄር ይሆናል ያለው ሁሉ ስለሚሆን፡ በዚያው ቦታ ሆኜ ነገሩ ሲፈጸም አየዋለሁ።

25 ዛሬ በተመሳሳይ ችግር ስላለች እናታችሁ እንዲህ ማሰብ ትችላላችሁ? በጣም ጥሩ፡ ማሰብ ከቻላችሁ፡ ትፈወሳለች። በጣም ጥሩ። ካመናችሁ፡ ቃሉን ተናግራችሁ ጠብቁት። አያችሁ? እመን፡ ጽና። ዘለአለማዊ ህይወት ነው።

26 አሁን፡ ነገ ከሰዓት... ለዛሬ፡ ልናገር የፈለግኩት ነገር ስለ አለ፡ የጸሎት ካርዶችን እንዳይሰጥ፡ ቢሊን ነግሬዋለሁ። በእውነት፡ እናገራለሁ፡ ከጥር ወር ጀምሮ፡ አገር አቋራጭ ስዞር ቆይቻለሁ፡ አሁን ግን፡ ወደ ቤት፡ ወደ ፎኒክስ፡ ተመልሻለሁ፡ እና (የሰውን ልብ ማንበቡ) ሙሉ ለሙሉ እስክዳከም ድረስ አንዳንድ ጊዜም ያለሁበትን እስክረሳ እያደረሰኝ ቆይቷል። ያስቀረልኝ ነገር የለውም።

27 ከዚያም፡ መውጣት ነበረብን፡ እነሱም... እናንተ ወንድሞች ጥቂት ቀናት ከእናንተ—ጋር እንድቆይ ጋበዛችሁኝ። በጣም አመሰግናለሁ። እዚህ ያሉ አገልጋዮች ምንኛ ድንቅ ናቸው ብየ ብዙ ጊዜ አሰባለሁ። ሕብረት የምናደርግበት ሰፊ ጊዜ ቢኖረን ተመኘሁ። ጌታ ቢፈቅድ፡ አንድ ቀን እመለሳለሁ። ሌሌላ ሳይሆን፡ ከአንዱ ቤተ ክርስትያን ወደ ሌላው በመሄድ እናንተን ሁላችሁ በከተማው ውስጥ ለመጎብኘት ብቻ ነው። እናንተ ብቻ ፈልጉን እንጂ፡ የእግዚአብሄር መንግስት ለመርዳት፡ ማድረግ የሚቻለኝን መስራት፡ ያስደስተኛል። አንዲት ቀን መጥተን እናንተም ከእኛ ጋር፡ በሆነ ስፍራ ጥሩ እና መልካም ጉባኤ እናሳልፋለን።

28 ደግሞም ወንድሞች ሆይ፡ እኔ ስለ እናንተ እንደምጸልይ፡ አትርሱ። አንዱ እርግጠኛ የምሆንበት ነገር ይህ ነው። እናንተ ሁላችሁ፡ እንድትጸልዩልኝ እፈልጋለሁ።

29 አሁንም—እኔ... ነገ ጠዋት በከተማዋ ባሉ መልከ መልካም አብያተ ክርስትያናት ጉባኤዎች ይካሄዳሉ።

30 ከጀፈርሰንቪል የሆኑ፡ ጥቂት ሰዎች እዚህ አሉ። አንዳንድ ጓደኞቼ፡ ከቤተ ክርስትያናችን ባለ አደራዎች አንዱ የሆነ፡ ወንድም ፍሬድ ሶዝማን፡ እዚህ አሉ። በጉባኤው ውስጥ ላየው አልቻልኩም ነበር። ከጀፈርሰንቪል የሆኑ ብዙዎች ወዳጆቼ፡ እና ወንድም... ኦህ፡ የተወደደው-... ጸሐፊየና—ሌሎችም፡ በጉባኤው ውስጥ አሉ። እስከ አሁን ድረስ አልታዩኝም።

31 እና ወንድሞቼ፡ በዚህ ከተማ እጅግ ድንቅ የሆኑ አብያተ ክርስትያናት አሉ። እና እንግዶች የሆናችሁ ሁላችሁ፡ ነገ አንድ ቤተ ክርስትያን መርጣችሁ ተካፈሉ። እርግጠና ነኝ፡ ይባርኳቸዋል። እንዲህ አይነት አገልግሎት የሚያምኑ ወንድሞች ናቸው። በመድረክ ላይ እና በጉባኤው መኃል የተቀመጡበት ምክንያት ይህ ነው፡ ስለሚያምኑ ነው። እኔም እነዚህን ሰዎች አመሰግናለሁ።

32 ጌታ ሆይ፡ ይህ በወንጌሉ ማሕበርተኞች—ስፖንሰር አድራጊነት የተከፈተውን የአገልግሎት ምዕራፍ ባርክልን። ይህ... ትክክል ይመስለኛል፡ ጉባኤውን ስፖንሰር ያደረጉት እነሱ ናቸው። እኔም—በግሌ በእነሱ ስፖንሰር አድራጊነት ብዙ ተጉዣለሁ፡ በዚያ ውስጥ ግን... መቼም እንዲህ መሆን አይገባንም፡ ብዙ ጊዜ ግን፡ ወንድሞች ትንንሽ ልዩነት ይፈጥራሉ፡ አንዱ **አንዲት ነገር** እንደሚያምን፡ ሌላኛውም፡ **አንዲት ነገር**፡ ከኋላችን ትንንሽ መቃቃር እና ምሬት ይፈጥራል፡ በዚህ ወቅት ግን መፈወስ አለበት፡ ደግሞ—እናንተም ብትሆኑ... ወይም እኔ፡ የውንጌሉ ሰራ ማሕበርተኞችን፡ ባገኛቸው፡ አንድ ላይ መተሳሰርን እንዲመጣ ይረዳል፡ ከዚያ አንድ እንሆናለን፡ ከዚያም በአንድነት ህብረት ይኖረናል፡ ልዩ ጊዜ ይሆናል። ስለዚህም እናመሰግናለን። እግዚአብሄር ምዕራፉን ይባርክልን። እግዚአብሄር በዓላማ እንደቀሰቀሰው ይሰማኛል።

33 እንዲሁም... የወንድም ኦራል ሮበርትስ ቦታ ለማየት መልካም አጋጣሚ ሆኖልኛል። የጴንጤቆስጤ—መታሰብያ ነው። በጣም ይገርማል፡ እጅግ ግዙፍ ቦታ፡ በጣም ያምራል።

34 ከዚያ በኋላም ወደ ወንድም ቶሚ ኦስቦርን ሄድኩኝ፡ የሱም ሌላ ድንቅ ቦታ፡ ድንቅ የእግዚአብሄር ሰው፡ እኔ እና... ወንድም ቶሚ በጣም እንቀራረባለን፡ እንዲሁም፡ ወንድም ኦራል ሮበርትስ፡ እጅግ ቅርብ ወንድማማቾች ነን፡ እንዋደዳለን፡ በእግዚአብሄር መንግስት ውስጥ ሰላለ ህዝብ ጥቅም አሰበን ሁሉንም ለማድረግ እየጣርን እንገኛለን።

35 ስለዚህ በከተማ ውስጥ ካሉት ጥሩ ሰዎች ጋር እነዚህም ደግሞ መኖራቸው በእውነት አመሰግናለሁ። እናንተ በጎች ድንቅ እረኞች አሏችሁ። ብየ፡ እንደው ብናገር ይቀላል። ጸሎቴ ጌታ ከእናንተ ጋር ይሁን ነው። ወንድሞች፡ የነገ ከሰዓት አገልግሎት... ስንት ሰዓት ይጀምራል? ሁለት-ተኩል። ምናልባት ሌሎች ጉባኤዎች እንዳይረበሹ አንድ—አንድ ወይም አንድ-ተኩል እዚህ ተገኙ።

36 አሁን፡ አስቀድመው ካልነገሯችሁ፡ ዛሬ ማታ ጥቂት መጽሐፍቶች ይዘዋል፣ የጉባኤ... ፎቶዎች፣ ቴፖች፣ ቅጂዎች እና ወዘተ፡ ይዘዋል፡ ይሸጡላቸዋል። ይሁን እንጂ በነገው'ለት በሰንበት ቀን፡ እንዲሸጧቸው አንፈቅድም። መጻሕፍትም ቢሆኑ ወይም ሌላ ነገር ነገ አይሸጥም። አንፈቅድምም...

ምንም’ኳ ብዙዎች፡ “እጅግ ተሳስተሃል… ” ቢሉኝ፡ በጭራሽ ፈቅደንላቸው እናውቅም።

37 ሸማግሌው ባባ ቦሰዎርዝ “ወንድም ብራንሃም፡ ሆይ፡ እዚህ ጋር ተሳስተሃል፡” ይለኝ ነበር፡ እኔ ግን እንደው—የሚሰማኝ (እያችሁ? )፡ በዚህ መንገድ ነው። አንድ ከፈለጋችሁ፡ ይሰጧችሁ፡ ከዚያ በላይ ግን… በሰንበት ቀን—እንሸጥም። አይሆንም። ይሄው ነው። እንዲህ የማምን ከሆንኩ፡ ልኖርበት ይገባል፡ ከራሴ ጋራ… መኖር ይገባኛል። አያችሁ? ከእምነቴ እና ከራሴ ነገር ጋር—መኖር አለብኝ… ወይም ቤት ድረስ ልካችሁ፡ መኖርያም፡ ድረስ፡ ወደ ቦታው ልካችሁ አግኙ።

38 እንደው፡ እሰኪ ዛሬ ማታ፡ እንደው፡ እሰኪ አለ የምንለው፡ የሰራ ነገር፣ ወይም ምንም ይሁን፣ የቀኑ ድካምም ይሁን እንርሳው። ነገር ሁሉ ወደ ጎን እንተወውና፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ቃሉን እንከታተለው፡ እግዚአብሄር በቃሉ አልፎ ምን እንደሚነግረን እንመልከት። እንደው ዛሬ ማታ እጅግ ድንቅ በረከት እንዲሰጠን ጌታን እለምነዋለሁ።

39 ጂን፡ ያቺን ልጅ አምጣልኝ’ማ? እሷን ልጅ ልትይዝልኝ ትችላለህ? ደሰ የምትል ሚጢጢ ናት አይደል? **እቺን** ከምታክለው ልጄ ሳራ ጋር ለመጫወት፡ ከእኔ ጋር ቤት መሄድ ትፈልጊአለሽ? ኦህ፡ ትፈልጊአለሽ? እኔ—እራሴም እፈልግሻለሁ። አንቺን ታክላለች፡ የአባቷ ሚጢጢ ናት። እህ-ህህም። ህህም። አንቺም—አባትሽን እንደምትወጂው አውቃለሁ፡ ትወጅዋለሽ አይደል? ማሚስ? ኦህ፡ አዎን ትወጃታለሽ። እዚያ ጋር ቁጭ ብላ፡ የምታትየኝ፡ በጣም ቆንጆ ልጅ። ዓይኖቿ በብርድ ልብስ መካከል በእሳት እንደተበሉ ሁለት ቀዳዳዎች ይመስላሉ—እና ቡኒ ጸጉር።

40 ህጻናትን እወዳለሁ። ቤት ውስጥ ሁለት ትናንሽ ሴት ልጆች አሉኝ። አንዷ ርብቃ ሁለተኛዋ ደግሞ ሣራ ትባላለች።

41 እና እጅግ እወዳቸዋለሁ። ሁለቱም የዳዲ ልጆች ናቸው፡ የሆነ ጊዜ፡ ወጥቼ ነበር፡ እና ታውቃላችሁ። እና እንደገባሁ ጀርባየ ላይ አዝየ እጫውታቸዋለሁ፡ እና… አሁን ግን ቤኪ ትልቅ ሆናለች፡ እኔን እክላለች አትታዘልም። ጀርባየን ትሰብራለች፡ ቢሆንም ግን… እሰከ አሁን ድረስ፡ የዳዲ ልጅ ናት። ምናልባት፡ በሚቀጥለው አመት፡ ከመንግሰት ትምህርት ቤት አርቀናት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እናስገባታለን።

42 እና፡ እናንተም እንደምታውቁት፡ አገልግሎት ላይ እቆያለሁ። ስለዚህ ዳዲ ቤት እሰኪገባ ድረስ፡ ይጠብቃሉ። ነገ ማታ በራሱ ቤት እሰክገባ ሌሊት ድረሰ ይጠብቁኛል። ስለዚህ፡ ማለዳ ሦስት ወይም አራት ሰዓት አካባቢ፡ እደርሳለሁ። በጣም ይደክመኛል እዝላለሁ፡ እናት ትመጣና ታስገባኛለች፡ እኔ… በዚህ መድረክ፡ እ… ቅባት… ሲኖር ደሰ ይላል፡ ሲተዋችሁ ግን ችግር ውሰጥ ትገባላችሁ። ሰንቶቻችሁ ይሄን ታውቃላችሁ? ታድያስ፡ በትክክል።

43 ተመልከቱ። ኤልያሰ ወደ ተራራው ወጥቶ ከሰማይ እሳት አውርዷል፣ ከሰማይ ዝናብ አውርዷል፣ መንፈስ በራቀው ጊዜ ግን፡ አርባ ቀናት ያህል በምድረበዳ ሲቅበዘበዝ እግዚአብሄር አገኘው፡ በዋሻ ውስጥም አቆየው።

44 ዮናስ ተወርውሮ በአሳ አንበሪ ሆድ ውሰጥ፡ ሶስት ቀን እና ሌሊት ቆየ፡ ወደ ዳርቻው ተተፋና በየዳርቻዎቹ እየሰበከ ሄደ። ከተማዋም በንስሃ ወደ

እግዚአብሄር ተመለሰች። ቅባት ከራቀው በኋላ ግን፡ ወደ ተራራው ራስ ወጣና እግዚአብሄር ህይወቱን እንዲወስድ ጠየቀ። አያችሁ?

45 በቅርብ ጊዜ፡ የጌታ እራት ሲኖረን የምንዘምረው መዝሙር የጻፈ ሰው፡ ዊልያም ኮውፐር መቃብር አጠገብ ቆሜ ነበር፡

> በደም የተሞላ የደም ፏፏቴ፤
> ከአማኑኤል ደም ስር እየፈሰሰ፡
> ሐጥያተኞችም ከምንጩ በታች ይንበረከካሉ...

46 ምን እንደገጠመው... ሰለሱ ሰምታችኋል? ያንን ምሪት ከራቀው በኋላ፡ እራሱን የሚያጠፋበት ወንዝ ፍለጋ ወጣ።

47 ቤቴ ከድሮው ኬንታኪ ቤቱ ማዶ ላይ ነው። ስቴፈን ፎስተርም እጅግ ታዋቂ የፎክ መዝሙሮችን ለአሜሪካ ያበረከተ ሰው ነው። ሲጽፍ፡ በምሪት ነው፡ በዚያ ምሪት፡ መዝሙር ይጽፋል፡ በተለየው ጊዜ ግን፡ ወጥቶ ይሰክራል። መጨረሻ ላይ፡ ሰራተኛውን ጠራትና ሰለት ተቀብሏት እራሱን አጠፋ።

48 ሰዎች በመንፈሳዊው ዓለም የሚኖር ሰው የሚያጋጥመውን ነገሮች አያውቁም። አሁን **እዚህ**፡ ተራራን እንደምታንቀሳቅሱ ያህል ይሰማችኋል። እሰኪ ቅባቱ ለቋችሁ ይሂድ፡ (እንደው፡ የሚመልሳችሁ ሰው ካጣችሁ'ማ) በዚያች ቅጽበት ይጀምራል፡ ከዚያ በኋላ፡ ምናልባት ለጥቂት ሰዓታት፡ የት እንዳላችሁ፡ ምንም ላታውቁ ትችላላችሁ። ከሌሊት ወደ ሌሊት፡ ዋና ነገራችሁን ይበላባችኋል።

49 እና ባጭሩ... ሰለ ህጻን ሣራ እና ርብቃ ልንገራችሁ። በማግስቱ ጠዋት፣ መተኛት አልቻልኩም፣ እና ተነሳሁ፣ ወንበር ላይ ተቀምጬ ነበር፣ እና ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቤኪ፣ ታላቅ ሰለሆነች፡ ከሣራ ይልቅ—እግሮችቿ ረዘም ይላሉ፡ ነቃችና፡ ከአልጋው ወርዳ፡ ቤኪ እየሮጠች... መጣች፡ ታናሽ እህቷን ሳትቀሰቅስ፡ ያላትን አቅም ሁሉ ተጠቅማ፡ እየሮጠች ወደ ቤቱ ብቅ አለች። እኔም አንዱ እግሬ ወደ ጎን ሰላደረግኩት፡ "ዳዲዬ፡ ዳዲዬ... " እያለች፡ ሚዛኗን ጠብቃ፡ ዘለለች። ታውቃላችሁ፡ ልክ እንደ—ዘመናዊቷ ቤተ ክርስቲያን፡ ታውቃላችሁ፡ ለብዙ መቶ ዓመታት በጨዋታው ውስጥ፡ ለረጅም ጊዜ ቆይታለች። ሚዛኗን መጠበቅ በትክክል ትችልበታለች፡ እና እጆቿን ወደ እኔ አዙራ እንዲህ አለችኝ፦ "ወይኔ፡ ዳዲ፡ ዳዲየ... "

50 እና ትንሿ ሣራ፡ በግርግሩ ውስጥ፡ ነቃች። ምናልባት፡ የእናንተ ልጆች ያድርጉ አያድርጉ፡ አላውቅም እንጂ፡ ታናናሽ ልጆቼ፡ የታላላቆቻቸው-ልብሰ-ይወራረሳሉ። ታውቃላችሁ፡ ሣራ የቤኪ ፒጃማ ለብሳ ነበር፣ እግሩ በጣም ረጅም ነው። እና፡ ትንሿና አጭር ወገን፡ እየወደቀች፡ እየተደናቀፈች መጣች። እና ትንሽ ዘግይታ፡ ደረሰች። ቤኪም ዘወር አለችና፦ "ሣራ እህቴ፡ አንድ ነገር ልንገርሽ፡" አለቻት። አየሽ፦ "መጀመሪያ እዚህ የነበርኩት እኔ ነኝ። እና ዳዲን በሙላት ይዤዋለሁ፡ ለአንቺ የቀረ ነገር የለሽም። ሁሉንም የእኔ ነው።"

51 አንዳንድ ሰዎች ሰለ ሃይማኖት ማሰብ የሚሞክሩት በዚህ መንገድ ነው፣ አይደለም እንዴ? ኧረ-እህ። በትክክል።

52 ምስኪኗ ሣራም፡ ትንሽ ከንፈሯን ጣለች፡ ጥቁቁር አይኖቿም ቀና ብለው አዩኝ፣ እና ማልቀስ ጀመረች። ቤኪም እወዳታለሁ። ጉንጯን ጉንጩ ላይ

አድርጋ፡ አቀፈችኝ። ቤኪ ዳዲን በሙላት ስለተቆጣጠረችው ሣራ መሄድ ጀመረች። እና ሌላኛውን ጉልበት **እንዲህ** ዞር አደረግኩላት፡ እና **እንዲህ** ተንቀሳቀስኩላት። ኦህ፡ ወድያውኑ ፈገግ አለችና፡ ሮጣ ጉልበቴ ላይ ዘለለች... ገና ጨቅላ ነበረችና እግሮቿ ወለሉን እንኳን መንካት አይችሉም ነበር። ትንሽ ጥገኛ ነበረች (ምናልባትም፡ እንደ እኔ ዓይነት፡ ጥገኛ፡ ታውቃላችሁ)፡ ወለሉንም አትደርስበትም... አትችለውም። ታውቃላሁ፡ ግዙፍ የሐይማኖት ተቋም አይደለችም፡ ስለዚህ ጠንካራውን ወለል መውረድ አትችልም። ዕድሜዋም ገና ነው ጨቅላ ናት።

53 ስለዚህ፡ ጥገኛ ነች፡ ሁለቱ እጆቼ **እንዲህ** ዘርግቼ ወደ እኔ አስጠጋኋት እና ጠበቅ አድርጌ አቀፍኳት፡ ጥቁር ዓይኖቿን ስልምልም እያደረገች፡ ርብቃን አየቻት። "ርብቃ፡ እህቴ፡" ብላ፡ እንዲህ—አለቻት፦ "ትክክል ነው አንቺ ዳዲን ሙሉ በሙሉ ይዘሽዋል፡ አንድ ነገር ግን እንድታውቂ እፈልጋለሁ፦ ዳዲዬ ሙሉ በሙሉ እኔን ይዞኛል።" ስለዚህ...

54 ይሄው... እሱ እኔን ይዞኛል። ትልልቅ ነገሮችን ለማድረግ ትምህርት ላይኖረኝ ይችላል፡ እኔ እስከማውቀው ግን፡ እንደ ጥገኛነቴ መጠን እሱ ይዞኛል፡ ብቻ ሁለት እጆቹ ይቀፉኝ፡ እኔ ደህንነት ይሰማኛል።

55 እሺ በቃ፡ ቃሉን ከመክፈታችን በፊት ሌላ ጥቂት የጸሎት ቃል እናሳርግ።

56 የሰማይ አባት ሆይ፡ እኛም አሁን፡ ልክ እንደ ልጆች መሆናችንን ተገንዝበናል። ከኛም—ጋር መሆን፡ እና ከእኛም ጋር ማምለክ ትወዳለህ። እኛም አንተን ስናመልክህ፣ አንተም ስትወደን፣ አቅፈህ ስትይዘን፣ መንፈስ ቅዱስ ላክልን፡ ህያው መሆንህን እና አባታችን እንደ ሆንህ አሳውቀን፡ እኛም አብዝተን እናመሰግንሃለን። አሁንም፡ መንፈስ ቅዱስ በዚሁ ማታ ወደ እኛ ይምጣ። ጌታ ሆይ፡ የሁላችንም ልብ ውደድ። መባረክን ባርከን። አባት ሆይ፡ የምሕረትህ ጠብታ እንደ ጤዛ ይውረድብን። ሐጥያታችንን አትመልከት። እጅግ ብዙ ናቸውና። ጌታ ሆይ፡ ይቅር በላቸው። አባት ሆይ፡ እናመልክህና፡ እናመሰግንህ—ዘንድ፡ እቤት ውስጥ እንደሚሯሯጡ፡ አባታቸውም እንደሚጠብቃቸው እንደሚያውቁ ልጆች እንሆን ዘንድ፡ ነፍሳችን—ቀድሳት፡ መንፈሳችንም ነጻ ትሁን፡ ጌታ ሆይ፡ ይቅር በለን፡ ወደ እጆችህ ተቀበለን፡ በሽታዎቻችንም—ፈውስልን። ጌታ ሆይ፡ አድርግልን።

57 አሁን፡ ይሄን አውቀናል። ቃል—መተርጎም ብቃት ያለው ሰው የለም። ዮሃንስ በዙፋን ላይ በተቀመጠው ሰው በቀኝ እጁ ላይ መጽሐፍ አይቷል፡ ይሁን እንጂ በሰማይ ቢሆን፡ ወይም በምድር፡ ወይም ከምድርም በታች መጽሐፉን ሊከፍት፡ ወይም ማሕተሙን ሊፈታ የሚችል ሰው አልነበረም። ከዚያ በኋላ ግን፡ ከዓለም ምስረታ በፊት እንደታረደ በግ አንዱ መጣ። እሱም የተገባው ነበር። መጽሐፉንም ወሰደ፡ ማህተሞቹን ፈትቶ፡ መጽሀፉን ከፈተ። አንተው በግ ሆይ፡ ዛሬ ምሽት ናልን። አባት ሆይ፡ እንጠብቅሃለንና፡ መጽሀፉን ክፈትል፡ የእግዚአብሄር በግ በሆነው፡ በኢየሱስ ስም ጸለይን። አሜን።

58 ለዛሬ ማታ፡ ባለ ሶስት ቃላት፡ የሆነች አነስ ያለች ርዕስ መርጫለሁ። ከዚያ በፊት ግን ከቅዱስ ዮሃንስ 11ኛው ምዕራፍ ከቁጥር 23 ጀምረን፡ አንድ ወይም ሁለት ቁጥሮችን እነባለሁ።

**ኢየሱስም፦ ወንድምሽ ይነሣል** አላት።

**ማርታም፡ በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ**... አለችው።

**ኢየሱስም፡- ትንሣኤና፡ ሕይወት... እኔ ነኝ፡ የሚያምንብኝ፡ በሞት እንኳ፡ ሕያው ይሆናል አላት፤**

**ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚያለሽን**?

**እርሰዋም፡ አዎን፡ ጌታ ሆይ፡ አንተ ወደ ዓለም** የሚመጣው **ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ እንደ ሆንህ እኔ አምናለሁ** አለችው።

59 እንደ ርዕስ፡ **ይህን ታምኛለሽን**? የሚለውን ባለ ሶስት ቃል እወሰዳለሁ፡

60 ከተወሰነ ጊዜ በፊት አንድ ታሪክ አንብቤአለሁ። ልብ ወለድ ታሪክ ይመስለኛል። አብዛኛዎቹ አገልጋዮች፡ ሁሉም ይመስለኛል፡ የዶ/ር ኢንግራሃምን—**የዳዊት ቤት አለቃ** የሚል መጽሃፍ አንበበዋል። በጣም ጥሩ መጽሐፍ ነው። እንደሚመስለኝ፣ ከህትመት፡ ፈጽሞ ጠፍቷል። ሰዎች እንዲጠቀሙት ለማድረግ፡ እንዲታተም እፈልጋለሁ።

61 በዚያ ውስጥ፡ አንዲት አንቀጽን አነበብኩ፡ ስለ አልዓዛር፣ ስለ ኢየሱስ፣ እና ስለ አልዓዛር እህቶች፡ ማርያም፣ እና ማርታ። በዚያም ኢየሱስ የኖረበትን አንብቤአለሁ፡ ከእነ ማርታ እና ማርያም ጋር፡ ይመስለኛል። ሁለቱም መልካም የዕብራውያን ሴቶች ነበሩ። አልዓዛርም የክሃናትን ሰርዓት ደብዳቤ ጸሓፊ ለመሆን፡ በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚማር ወይም የሚያጠና ሰው ነበር።

62 ኢየሱስም ከአልዓዛር ጋር፡ በተለየ መልኩ ወዳጁ ነበር። ወደ ቤታቸው በደረሰ ጊዜ መጽሀፍ ውሰጥ ሰናነብ፡ ማርታም ቃሉን ለመሰማት ዘግይታ፡ ማዕድ ለማዘጋጀት እራት በመሰራት ተጠምዳ፡ ማርያም ግን ከእግሩ ሰር ነበረች። ኢየሱስ ግን ማርያም የተሻለውን መምረጧን መሰከረላት።

63 ደግሞም፡ ኢየሱስን ወደ ዮሃንስ ያመጣው አልዓዛር እንደነበረ፡ **የዳዊት ቤት አለቃ**... በሚለው በዶ/ር ኢንግራሃም መጽሀፍ፡ ተነግሮናል። ሆኖም፡ ይህ እውነት ላይሆን ይችላል፡ እኔ አላውቅም፡ ለመነሻ ያክል ብቻ ነው፡ አብሯቸው ይኖር እንደነበረ ግን ይናገራል።

64 ኢየሱስ በቅዱስ ዮሃንስ 5:19 ላይ፡ የተናገረውን፡ በሚቀጥለው ሳምንት፡ ማለቴ ባለፈው ሳምንት፡ ሰንማረው ቆይተናል፣ "እላችኋለሁ... አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ፡ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ፡ ምንም አይችልም። አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና።" እያችሁ? "አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ።"

65 ሰለዚህ ታሪኩን ህያው ለማድረግ፡ አብ፡ ማለት እግዚአብሔር አሰቀድሞ፡ ልጁን፡ ኢየሱስን፡ እንዲህ፡- "ወዳጅህ፡ አልዓዛር፡ ይሞታል፡ ሞቱ ግን ለመልካም ነውና፡ ከቤት ርቀህ ሂድ ሊለው ይገባል። እንድትጸልይለት፡ ወይም፡ እንድታድነው፡ እጠራሃለሁ፡ አሁን ግን—ልታደርገው አልፈልግህምና፡ ለጊዜው ሂድ።" አብረን ሰንቀጥል ታሪኩን የምትመለከቱ ይሆናል፣ እውነቱ እሰከዚያው ድረስ ሲደራረብ ታዩታላችሁ። ሰለዚህ፣ ኢየሱስ፣ ሳይነግራቸው ወይም ምንም ነገር ሳይላቸው፣ ከቤት ወጥቶ ወደ ሌላ ቦታ ሄደና፡ በዚያ ምሽት

አልተመለሰም። ወደ ሌሎችም ከተሞች ሄደ። እና ኢየሱስ ከቤት እንደወጣ፣ ችግር ተፈጠረ።

66 ኢየሱስ ከቤታችሁ ሲወጣ፡ ችግር መንገዱን ይጀምራል። እሱ ቤታችሁን ለቆ ሲሄድ፡ ችግር መንገድ ላይ እንደሆነ፡ አስታውሱ። በቤተክርስትያናችሁ ውስጥ ማሕበራዊ ተቋማት እና ሌሎች ነገሮች ሁሉ በትክክል ሲሳተፉ፡ እንደ'ነ ባለ አሰራ ሰድሰቱ ሲሊንደሩ ሪክንቤከር የመሳሰሉ፣ ኢየሱስን ችላ ያሰብሏቸዋል፡ ኢየሱስ ከቤተክርስትያናችሁ ሲለይ፡ መከራ መንገዱን ይጀምራል። ወዳጄ ሆይ፡ አንድ ሐይማኖት፡ ኢየሱስ ጥሏት ሲወጣ፡ እሱን ችላ በማለት እንዲህ ሲሉት፦ "እኛ፡ አሁን እነኚህ ነገሮች ትክክል ናቸው ብለን አናምንም፡" በእሱ ፋንታ ሌላ ነገር ጋር ሲዳቀሉ፡ መከራ ይጀምራል። ይሄን አትርሱ።

67 በሉቃስ መጽሐፍ የሚገኘውን፡ የጌታ ኢየሱስን ታሪክ ያስታውሰኛል። ታውቃላችሁ ገና የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሳለ፡ የጴንጤቆስጤ በዓል ለማክበር፡ በየ ዓመቱ መሄድ ልማድ ስለነበራቸው፡ ቤተሰቦቹ ይዘውት ሄደው ነበር። በኢየሩሳሌም በዓሉን እያከበሩ በከተማው በነበሩ ጊዜ መልካም ጊዜም ካሳለፉ በኋላ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው፡ ትተውት የሦስት ቀናት መንገድ ተጓዙ። ምናልባት ኢየሱስ፡ ከዘመዶቻችን መካከል ይሆናል ብለው አሰበው፡ እንደ ቀላል ነገር አድርገውታል። አሁን፡ እኛ እንዲህ ማድረግ አይገባንም። እሱን ፍለጋ በዘመዶቻቸው መካከል በመጡ ጊዜ ግን፡ አላገኙትም።

68 እኛ ሜቶዲስቶች፣ ባፕቲስት፣ ፕሪስባይቴሪያን፣ ጴንጤቆስጤ፣ ስለሆንን ብቻ እንደ ቀላል ነገር መውሰድ አይገባንም፣ ወይም ቅድመ አያቶቻችን፡ ታላላቅ አማኞች ስለነበሩ፡ እንደው፡ የኢየሱስ ከእኛ ጋር መሆን፡ ቀላል አርገን እናስበዋለን። እንዲህ ማሰብ የለብንም። በየደቂቃው እና በየቀኑ ከእሱ ጋር ህብረት ሊኖረን ይገባል። ኑህ፡ ይሄ ደስ ይለኛል።

69 እግዚአብሄርን በአሁንነቱ እፈልገዋለሁ። ቤተሰቦቼ የነበራቸው፡ ወይም የአባቶቼ የነበረ ነገር፡ ድንቅ ነው፡ ወይም (የእነርሱ ነገር መልካም ነው።) እኛ ግን መንገዱን እጅግ አራርቀነዋል።

70 ዛሬ ምን እንደሆነ እንመልከት። ወደ ኋላ መለስ ብዬ አቶ/ ሙዲ ያደረገውን ማየት አልፈልግም፡ ምክንያቱ እኛ ከአቶ/ ሙዲ በተለየ መንገድ ላይ ነንና። የአብያተ ክርስትያኖቻችን ችግር፡ ወደ ኋላ መለስ እንልና፦ "መልካም፡ እስቲ ሚስተር ጆን ዌስሊ የተናገረውን፡ አንዳንዶቹ ምን እንዳሉ እንይ እንላለን።" ሐይማኖት በዘርፉ ካለው ደረጃ ይልቅ፡ ሳይንስ በመስኩ እጅግ የላቀበት ምክንያት ይህ ነው።

71 የዛሬ ሶስት መቶ ዓመታት በፊት፡ አንድ ፈረንሳዊ ሳይንቲስት በሰዓት ሰላሣ-አምሥት ማይልስ ፍጥነት ከተጓዛችሁ፡ የምድር ስበት ከምድር እንድትንሣፈፉ ያደርጋል በማለት አረጋግጧል። ሳይንስ ዛሬ በአሁኑ ወደ ኋላ ተመልሶ ያሄን የሚያጣቅስ ይመስላችኋልን? በሰዓት ሺህ ዘጠኝ መቶ ማይልስ ደርሷል ይቀጥላሉም። ፊታቸው ያለውን እየተመለከቱ፡ እየቀጠሉ ይገኛሉ። እኛ ግን ወደ ኋላ መመለስ እንፈልጋለን ሙዲ ወደ ተናገረው፣ ሳንኪ የተናገረው፣ ፊኒ

የተናገረው፣ ኖክስ፣ ካልቪን፣ ሌሎቹም። የተናገሩት ነገር ትክክል ነበር፡ ያ ለዘመናቸው ነው። እኛ ግን እንቀጥላለን።

72 እያቴ የበሬ ጋሪ ጋለበ። እኔ ፎርድ ቪ8 እየነዳሁ ነው። ልጄ ጄት አውሮፕላን ያበርራል። ይሄ ነው፡ እየቀጠልን ነን። ሐይማኖት መሆን ያለበት እንዲህ ነው። የጌታ መምጣት ቀርቧል። ቤተ ክርስቲያን ወደ ሥልጣናቸው መቀጠል አለባት። ሳይንስ የቻለውን ያህል ወደ ላይ ይወጣል ከዚያ በኋላ ግን ይወርዳል፡ እኛ ግን ያልተዳሰሰ ምንጭ አለን፡ እኛ ልንደርስበት የተገባ፡ ገና ያልተነካ፡ ያልተገደበ፡ የእግዚአብሄር የሆነ፡ ስልጣን አለ። እኛ ግን እንደ ክርስትያን፡ ለመኖር ከታሰበልን ሐሳብ ከአንድ ሚልዮን ማይልስ በታች ርቀን እየኖርን እንገኛለን። በራሴ እጅግ እፍራለሁ፡ እነዚህን ተቋማት ሳያቸው፡ በሽታውም፣ አሁን ያሉ መከራዎች ሁሉ ሳይ ያሳፍረኛል። ይሄኔ'ኮ ቤተ ክርስትያናችን፡ በየመንገዱ በሽተኞችን መፈወስ፣ ሙታንን ማስነሣት፣ ዲያብሎስን መገሰጽ፣ ድንቅ እና ተአምርን በማድረግ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ህያው መሆኑን ለዓለም ማሳየት ነበረባት። ማድረግ የሚገባንም ይህ ነው።

73 ለምን፡ እናንተ የምትሉት፦ "አቶ/ ሙዲ በፍጹም... " አቶ/ ሙዲ በዚህ ዘመን አልኖረም። አዎን። እኛ ጌታ በሚመጣበት ዘመን እየኖርን ነን። እሱ ከዘመዶቻችን ጋር መኖሩ እንደ ቀላል ነገር አርገን እንቆጥረዋለን። በቀደም ለት ፈታኝ አቶ/ ግራሃምን በፈተነው ጊዜ ግን፡ ከዘመዶቻችን መካከል አለመኖሩ ተረዳን።

74 የት አገኙት? ኢየሱስን የት—የት አገኙት? እዚያው እርሱን በተዉት ቦታ። የት ነው የተዉት? በበዓለ ኃምሣው በእል። ቤተክርስትያን ኢየሱስን የት፡ የት ተውነው? በበዓለ ኃምሣ በእል። ከጥንታዊው የበዓለ ኃምሣ ኃይልና ከበዓለ ኃምሣው በእል ስንርቅ፡ ከኢየሱስ እንርቃለን። ወዳጆች ሆይ፡ ይህ እውነት ነው። ከታሰበልን በታች እየኖርን ነን። አዎን፡ ወዳጆቼ ሆይ።

75 እነርሱም በበዓለ ኃምሣው ተውት፡ ስለዚህ ሜቴዲስቶች፣ ባፕቲስቶች፣ ፕረስቢተርያኖች፣ እና ጴንጤቆስጣሎች እሱን የሚያገኙበት ብቸኛው ስፍራ፡ እርሱን ወደተዋቻሁበት በመመልስ ብቻ ነው። የጌታ ደስታ ወዴት አለ? የጌታ ኃይልስ ወዴት ነው? ቤተ ክርስትያን ዛሬ ትጠይቃለች፦ "ታሪክ ሰሪው እግዚአብሄር ምን—ምን ገጠመው? " እሱ'ማ ህዝቡ እስኪጠሩት ድረስ በስፍራው ሆኖ ይጠብቃል። ነገር ግን...

76 በሐይማኖት ተቋማት ስር ብንሆን አይሆንም። ከሳይኮሎጂ ስር ሆነን አይሆንም። በሂሳብ ስሌት ልንሰራው አንችልም ወይም በትምህርት ልንሰራው አንችልም። እራሳችንን እንለያያለን፡ እራሳችንን እንከፋፍላለን። እኛ አልተከፋፈልንም። እኛ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ነን። ሁላችንም በክርስቶስ አንድ ነን፣ የሐይማኖት ተቋማት በፍፁም አያደርጉም። ምንም ጥሩ ቢሆኑም፡ አያደርጉትም። የወንጌል ትልቁ እንቅፋት ትምህርት ነው፡ ትምህርታችን ነው።

77 የሚያስፈልገን ትምህርት አይደለም። ኃይሉን ለመሥራት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እና ሥራ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያስፈልገናል። ኢየሱስ፦ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂድ—አስተምሩ" አላለም። "ወደ ዓለም ሁሉ ሄዳችሁ... እንዲህ አርጉ" በፍጹም አላለም፤ እሱ ያለው፦ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ እና ወንጌልን ስበኩ

ነው።” ወንጌል ማለት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል፡ ወይም ትንሣኤን፡ ለማስረዳት ነው። አሁንም ግን መሆን ከሚገባን ሚልዮን ማይሎችን አንሠን እንገኛለን። ወደ ፊት እንዘርጋ። እሱን ትተን ወደ ሄድንበት ወደ በዓለ ኃምሣው እንመለስ።

78 ኢየሱስ፡ በዮሃንስ፡ 15ተኛው ምዕራፍ፡ ይመስለኛል፦ “እኔ የወይን ግንድ ነኝ፡ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፡” ብሏል። ስለዚ አሁን፡ ይህ የወይን ግንድ የመጀመርያውን ቅርንጫፍ ቢያበቅል፡ ከዚህ ቅርንጫፍም የሐዋርያት ስራ መጽሐፍ ቢጻፍ፡ ሁለተኛው ቅርንጫፍ ሌላ የሐዋርያት ስራ መጽሐፍ ይጻፍበታል። ሶስተኛው ቅርንጫፍም ሌላ የሐዋርያት ስራ መጽሀፍ ይጻፍበታል። ከዚያ ወይን የሚወጣ ቅርንጫፍ ሁሉ እንደ መጀመሪያው ቅርንጫፍ ይሆናል።

79 አሁን፡ እንደምናውቀው፡ ማዳቀል ይቻላል። በላዩ ላይ ሰምንት የሚያህሉ የፍራፍሬ ዓይነቶች ያለበት የሲትረስ ዛፍ አይቻለሁ። በብርቱካን ዛፍ ላይ የወይን ዘለላ፣ ሎሚና፣ ሌሎችም ጭምር አይቻለሁ፡ እነዚህ ሁሉ ግን የተዳቀሉ ነበሩ።

80 የዚህ ዘመን ችግርም ይህ ነው። ከገዛ ሐሳባችን ጋር፡ እና ከሐይማኖት ተቋሞቻችን ጋር ተዳቅለናል፡ ዛፉ ግን የራሱ የሆነ፡ ሌላ ፍሬ ቢያፈራ፡ ወደ ምንጩ እንደገባው እንደ መጀመሪያው ወይን ይሆናል። ሀሌሉያ! አቤት፡ ቤተ ክርስትያን አንድ ላይ መጣመራቸው አይቀርም፡ እኛ የምንፈልገው ግን የምንጩ ኃይልን ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሳኤው ኃይል፡ መንፈስ ቅዱስ ያስፈልገናል። አድርጉት ያለንም ይሄን ነው።

81 “እኔ የወይን ግንድ ነኝ፡ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ።” የወይን ዛፍ አንድ ቅርንጫፍ ቢያወጣና፡ ሰማያዊ የወይን ዘለላ ቢያፈራ፡ ቀጥሎ የሚበቅለው ወይንም የሚያምር ሰማያዊ ዘለላ ያፈራል። አስቀድሞ የወጣ ወይን፡ ከመንፈስ ቅዱስ አገዛዝ ስር ሆነው፡ ታላላቅ ተአምራቶችን፡ ምልክቶችም ሰርቷል፡ ምስክርነታቸውንም ለዓለም አትሟል... ብዙዎቹም በራሳቸው ምስክርነት፣ በገዛ ደማቸው፡ ምስክራቸውን፡ አትመዋል። ሁሉም ወንጌል ባመጣው አደጋዎች እና መሰል ነገሮች ሁሉ አልፏል። ተሰቃይተዋል፡ ተደብድቧል፡ ተቀጥቷል። “ሌሎች ሽልማቱን ለማግኘት ሲታገሉ፡ በደም ባሕር ሲቅበዘበዙ፡ ምቹ በሆነ በአበባ አልጋ ላይ፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት መወሰድ አለብን ወይ? ” የሚጠበቅብን ነገር ምንድነው? “መንገሥ ካለብኝ መታገል አለብኝ። ጌታ ሆይ፡ ድፍረትን ጨምርልኝ።” በእርግጠኝነት። እኛ የሚያስፈልገን...

82 እኛ አዲስ የሐይማኖት ተቋም አያስፈልገንም። ወይም አዲስ የቤተክርስትያን ህንጻ አያስፈልገንም። እኛ የሚያስፈልገን ሐጥያትን-የሚገድል በበዓለ ሐምሳ የተወለደ የጥንቱን-ዓይነት ምሽግ፡ እና የጠራ-ሰማይ፡ እንደገና ወደ ቤተ ክርስትያኒቱ የተመለሰው፡ ኢየሱስን ወደ መድረክ የሚያመጣውን፡ የመንፈስ ቅዱስ ሪቫይቫል ሐይል ነው።

83 ይህ ታሪካዊ አምላክ ሁሌም በወሳኝ ጊዜ ወደ መድረክ ይወጣል። ይህ ያስፈልገናል። ዛሬ የአብያተ ክርስትያኖቻችን ችግር ይህ ነው። ወደ ኋላችን እጅግ ርቀናል። በዓለም ፋሽኖች መውደቅ ጀምረናል። ቀስ በቀስ፡ ዓመት ከዓመት፡ በየጥቂቱ እየሞተ ፈጽሞ ጠፍቷል።

84 በቅርብ የመከርከም ጊዜ ይሆናል። የእኔ በዚህ መድረክ መቆም እርግጥ እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሔር በእርግጠኝነት ይከረክማታል። ፍሬ እንድታፈራለት እግዚአብሄር ይከረክማታል። በእነዚህ ቀናት የዓለምን ስራ ከላይዋ ይቆርጣል። ቤተክርስትያን በሰመ ሐይማኖት የተጓዘችው ጉዞ፡ እጅግ አሰጸያፊ ነው።

85 ስለዚህ፡ ኢየሱስ በሄደ ጊዜ፡ ሞት ሲገባ ተመልክተናል። ኢየሱስ ከቤተ ክርስትያናችን ሲለይ፡ የመንፈስ ቅዱስ ሀይል ከቤተ ክርስትያናችን ይርቃል፡ መንገዳገድም ትጀምራለች—እና ትሞታለች። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትርጉም አልባ ትሆናለች። አሁን፡ ኢየሱስ በተለያቸው ጊዜ፡ ሞት ገባባቸው። አቤት፡ ከባድ የሐዘን ጊዜ ነበር።

86 ደግሞም አስታውሱ፡ ኢየሱስን እዚያም እዚህም ፈለጉትና፡ መልዕክት ላኩበት፡ እሱ ግን አልመጣም። በድጋሚ ላኩበት፡ አሁንም አልመጣም፡ እሱ ግን ምን እንደሚያደርግ ያውቅ ነበር። እሱ ዛሬ ማታም፡ የሚያደርገውን ያውቃል። በእርሱ ዘንድ የሚጠፋው ነገር የለም፡ ምን ሊያደርግ እንዳሰበ በትክክል ያውቃል። እኔ በዚህ መድረክ መቆሜ እርግጥ እንደሆነ ሁሉ፡ ዛሬ ከፍ የሚያደርጋቸው ሰዎች አሉት። ሰለ ሰሙ ከአሕዛብ ዘመን የሚያነሣው ህዝብ አለው። ደግሞ ይፈጽመዋል።

87 መጪው ጊዜ የአይሁድ ዘመን ነው፡ አሕዛብ ግን ከእርሱ ስለራቁ፡ ዘመናቸው ወደ ማለቂያው ደርሷል። ክርስቶስን ተቃውመውታል፡ ምልክቶቹን ሁሉ ተቃውመዋል፡ የእግዚአብሄር የሆነውን ሁሉ በመቃወም፡ ቴሌፓዚ ነው ወይም አጋንንታዊ ነው በማለት ሰያሜን ሰጥተውታል… መንፈሰ ቅዱስን በመሳደብ እራሳቸውን ከእግዚአብሄር አርቀው በማተም ይገኛሉ። እግዚአብሄር ግን ታናሺቱን መንጋ አንስቶ፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ኃይለኛ ቤተ ክርስትያን ያደርጋታል፡ ከዚያ በኋላም መንፈሱን ወደ አይሁድ ይመልሰዋል፡ የአሕዛብ ቤተክርሰትያን ግን ወደ ቤት ይወሰዳታል። ፍጹም እውነት ነው። አሁን በመሠራት ላይ ናት። መቼም፡ በዘመን ፍጻሜ፡ ደጅ ላይ ደርሰናል።

88 ኢየሱስ፡ አስቀድሞ አውቋል። ከጥቂት ቀናት በኋላ “ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቷል፡” አላቸው።

89 ለምን፡ ደቀ መዛሙርቱ ግን ትንሽ እረፍት እንደመውሰድ አርገው አሰቡት። “ደህና፡ ተኝቶስ ከሆነ፡ ተሽሎታል ማለት ነው፡” አሉ።

90 ስለዚህ፡ ያውቁ ዘንድ፡ በሚገባቸው ቃላት… እንዲህ ብሎ ነገራቸው አላቸው፡ በቃ፦ “እሱ ሞቷል፡ ሰለእናንተ ግን እኔ በዚያ አለመኖሬ ደሰ ይለኛል አላቸው።” እያችሁ? “ሰለእናንተ ግን፡ እኔ በዚያ አለመኖሬ ደሰ ይለኛል።” ምክንያቱ እነሱ እንዲፈውሰው—እንዲፈውሰው—በማለት ይለምኑት ነበር፡ እሱ ግን ሊፈውሰው እንደማይችል ያውቃል፡ ምክንያቱ ራዕዩ ገና ነበር… እብ የነገረው ጊዜ ያውቀዋል ከአራት ቀናት በኋላ ነው። በመቅብር አጠገብ ሆኖ፡ እንዲህ ሲል እንዴት ያምራል፦ “አባት ሆይ፡ ሰለሰማከኝ፡ አመሰግንሃለሁ፡ ነገር ግን በዙርያዬ ሰለቆሙት ይሄን ብያለሁ።” እያችሁ? ምን ሊያደርግ እንደሆነ አሰቀድሞ ያውቅ ነበር። “እንድቀሰቅሰው እሄዳለሁ፡” ብሏልና።

91 አሁን፡ የቤት ጧሪ ሰለሞተ፡ ሐዘን ሆኗል። ያቺ ምስኪን ቤተሰብ እጅግ እንደተሰባበረች አሰባለሁ። ያዘነ ቤት እና ያዘነች ልብ ሲኖራችሁ፡ ኢየሱስ ቅጽበት ሲደርስላችሁ፡ አቤት ደሰ ሲል፡ አይደለም’ዴ? ምስኪን ማርታን

ሳሰባት፡ ቆንጆዋ እመቤት፡ ጥቁር ሻሽ ፊቷ ላይ ጣል አርጋለች፡ ምስኪኗ ማርያምም፡ እርስ በእርስ ተቃቅፈው፡ እንዲህ ሲሉ፦ “አሁንስ ምን ይውጠናል? አባት እና እናታችን ሞቷል፡ ውድ ወንድማችንም እንዲሁ… አሁን፡ ከቤተ ክርስትያን ወጥተናል፡ ከመካከላቸው አውግዘውናል፡ የናዝሬቱን ኢየሱስ ለመከተል ከነሱ ተለየን። እርሱ ግን የት እንደሄደ፡ ነቅሎ ወጥቶ ርቆናል።”

92 አንድ ተቺ መጥቶ እንዲህ ሲል ይሰማኛል፦ “ሄይ፡ ያ መለኮታዊ ፈዋሽ፡ ያ የገሊላ ነቢይ የት አለ? አሁን ታድያ የት ገባ? አየሽ፡ ማድረግ የሚገባው ነገር ሲኖር አሁን ጠፋ።” ይሄ ነው። እያችሁ፡ እግዚአብሄር እንዲህ ማድረግ ይወዳል፡ ሰዎችን፡ በቃ፡ ሰዎች ማንነታቸውን እንዲረዱ ማድረግ ይወዳል፡ አዎን፡ ምን እንደሆኑ በትክክል እንዲረዱ ያደርጋቸዋል። በረከትን የሰጣቸዋል። ይገለጣል፡ እራሱን ያሳያል፡ እራሱን ከሕዝቡ ጋር ያስተዋውቃል፣ ይህም ምን አይነት ግብረ መልስ እንደሚሰጡ ለማየት፡ ምን እንደሚያደርጉ ለማየት ነው።

93 አሁን፡ ከጥቂት—ቀናት በኋላ፡ ለአራት ቀናት፡ ምስኪኑ አልዓዛር፡ መሞቱን እንረዳለን። ወሰደው ቀበሩት። ሁለተኛ ቀን፡ ሶስተኛ ቀን፡ አራተኛው ቀን… መበሰበስ የሚጀምረው በሶሶተናው ቀን እንደሆነ፡ ሰው ሁሉ ያውቃል፡ ከሁሉ በፊት፡ አፍንጫ ፊት ላይ ይወድቃል። ወያውም መበሰበስ ይጀመራል፡ የቆዳ ትሎች ሰውነትን መብላት ይጀምራሉ። መሬት ውስጥ አስገቡት፡ እሱ ባስተኙበት በዋሻው ላይም ታላቅ ድንጋይ አኖሩበት። ወጣት ሴቶቹም፡ በየጊዜው ወደ መቃብሩ ሄደው ተንበርክከው ያነባሉ።

94 ከጥቂት ቀን በኋላ፡ “ኢየሱስ መጥቷል። ወደ ከተማው ሲገባ አይተነዋል።” የሚል ዜናው መሰራጨት ጀመረ። እቤት፡ ያቺ ትንሽ ሰው ማርታ፡ ቅስስ ብላ፡ ፈዛዛ መስላ የነበረች ሴት፡ ከምን እንደተሰራች ማሳየት ጀመረች። ይሄው ወጣች። እሱን ፍለጋ፡ በሩጫ ወደ አደባባይ ወጣች። አንዳንዶቹ በመንገድ ዳር፡ “እሁንስ፡ መቼም ሐይማኖታችሁ ውሸት እንደሆነ፡ ተረድተሽ ይሆናል፡” ሲሏት ይታየኛል። ትችቶቹን ሁሉ ረጋግጣ፡ ንቃ አለፈች። እስክታየው ድረስ፡ ምናልባት በአንድ ጎዳና ላይ ቁጭ ብሎ ይሆናልና ፍለጋዋን ቀጠለች።

95 አሁን፡ እሷ′ኮ… እሱን ለመውቀስ—ክፋ ቃላት ልትናገረው የሚያስችላት፡ ምክንያት ነበራት። እሷ ሄዳ፦ “አንተ፡ ሰማኻ′ማ፡ ሰማኻ′ማ። አንተን ብሎ ነብዩ፡ አንተን ብሎ የእግዚአብሔር ሰው። ስንጠራህ ለምን አትመጣም? ለምን፡ አሁን የከተማይቱ መሳቂያ ሆነናል። አንተን ለመከተል′ኮ ነው ቸርቻችንን ጥለን የወጣነው።” ለማለት መብት ያላት ይመስላል። ይሁን እንጂ፡ **በጉ እና ርግብ**፡ ብየ እንደሰበኩት፡ በግ ከሆንን፡ በግ መብቱን ሁሉ ይተዋል። ትክክለኛ አባባል ነው። ከሱፍ ሌላ አንዳች የለውምና፡ መሰጠት አለበት። እናንተም ጌታን ለማገልገል መብቴ የምትሏቸው ነገሮች ሁሉ መተው ይጠበቅባችኋል። ትክክል ነው።

96 የተቦጫጨቀ ልብሶችን የሚለብሱትን ሴቶች እየተከታተልኳቸው ነበርና፡ ምን እንዳሉኝ፡ ታውቃላችሁ፦ “እንዴ፡ እኛ′ኮ—አሜሪካውያን ነን። የፈለግነውን ነገር ማድረግ እንችላለን።”

97 እኔም፦ “አዎን ትክክል ብላችኋል፡ በግ ከሆናችሁ ግን፡ መብቶቻችሁን ትተዋላችሁ” አልኳቸው። ለአንድ ሴት ሲጋራ እያጨሰች፡ እንዲህ አይነቱ ህይወት እንደመኖር የከፋ ነገር የለም። በትክክል ትክክል ነው።

98 በቅርብ ጊዜ አንዲት እመቤት፡ ከእኔ ጋር ስታወራ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ግን’ኮ፡ ሌላ ዓይነት ልብሶች አያመርቱም፡” አለችኝ።

99 እኔም፦ “የልብስ ስፌት ማሽን እና ሌላ ሌላ ዕቃዎች ግን ይሸጣሉ። ለዚህ ምንም ዓይነት ምክንያት አይሰጥበትም።” በትክክል ትክክለኛ ነው።

100 አስታውሱ፡ ምናልባት ለባሎቻችሁ ታማኞች ልትሆኑ ትችላላችሁ፡ አንድ ቀን ግን፡ በዝሙት ምክንያት፡ በርግጥ ትጠየቁበታላችሁ፤ “ሴትን አይቶ የተመኛት ሰው ሁሉ፡ በልቡ ከእሷ ጋር ዝሙትን ሰርቷል።”

101 እኔ የሚገርመኝ፡ የዛሬ ጴንጤ ሴቶች ምን ነክቷቸው ነው። ከጥንታዊው የመታረም ስሌት እንዴት ፈቀቅ አላችሁ። እናቶቻችሁ’ኮ ረዣጅም ጸጉር ነበራቸው፡ የዛሬ ጴንጤ ሴቶች ግን እንደ ማርዲ ግራስ ቀን ይቀባባሉ፡ ጸጉሮቻቸውን ይቆራርጣሉ፡ እንደሌሎቹ አካሄድ… አጫጭር ልብሶችን እንዲህ ይለብሱና፡ ወንዶች በሚያልፉበት ከሰዓት ጠብቀው፡ ግቢውን ለማጽዳት ይወጣሉ፡ ሴቶች ሆይ፡ ገብቷችኋል፡ ከእነዚያ ወንዶች ጋር ዝሙት እንዳደረጋችሁና ተጠያቂ እንደምትሆኑ ተረድታችኋል? ምክንያቱ እራሳችሁን ለዚያ ዓላማ ስለጋበዛችሁ። በቤተ ክርስትያን እና በህዝቡ ዘንድ እንዲህ አይነቱ ክፉ መንፈስ አለ፡ እነርሱ ግን አላወቁትም። ታውረዋል አያውቁትም። እውነት ነው።

102 ምናልባት እንደ ወንጌላዊ ይሄን ለመናገር መብት የለህም ትሉኝ ይሆናል። እንግዲህ፡ እኔ ማለት የምችለው—መንፈስ ቅዱስ የመራኝን እላለሁ፡ ብቻ ነው። እናንተ ሰዎች… በፍርድ ጊዜ ካገኘኋችሁ፡ ከደማችሁ ንጹህ ነኝ። የሰይጣን ከሆነ ምድራዊ ነገር ሁሉ ተለዩ። ራቁ። ተለዩ። ምንም ዓይነት የቴሌቪዥን ስታር ብትሆኚ አይገደኝም… አንቺ፡ እዚህ፡ የቴሌቪዥን ስታር አይደለሽም፡ አንቺ የእግዚአብሄር ልጅ ነሽ።

103 በቀደምለት በአንድ ፓስተር ቤተክርስትያን፡ ስለ ባርያ ንግድ ሰብኬ ነበር፡ ድሮ ባርያዎች ይሸጡ ነበርና። ሰዎች ይመጡና በጨረታ ይገዙአቸው ነበር። እነዚያ ሰዎችም፡ ከእንግዲህ ወዲህ፡ ወደ ትውልድ አገራቸው በፍጹም ስለማይመለሱ፡ ያለቅሳሉ፡ ያነባሉ። ደግሞም በአለንጋ ይገርፏቸዋል። መኪና እንደሚገዙ ግብይት ይገበዩአቸዋል፡ ዝም ብሎ እንደ ተራ ዕቃ፡ የሰው ልጆችን፡ በዋጋ ይሸጧቸዋል።

104 እና አንድ ቀን፡ አንድ ገዢ ደላላ፡ ወደ ትልቅ ድርጅት-… ማለቴ፡ ወደ አንድ ትልቅ ማሳ መጣና። “የሚሸጡ ባርያዎች አሉህ’ዴ? ” በማለት ጠየቀ፡

105 “አዎን፡ ለልውውጥ የተዘጋጁ አሉኝ፡” አለው። ተለቅ ተለቅ ያሉትን መግዛት ይፈልጋሉ። እነዚያን አባት፡ እና እናቶችን ይወስዱና… ያጋባት ሴት ምናልባት ደከም ያለች ከሆነች፡ ጠንከር ጠንከር ያሉትን ወንዶች ይወስዱና… ልክ እንደ ፈረስ እና እንደ እንስሶች ያራቧቸዋል። ፍጹም ሐጥያት ነው። እግዚአብሔር ሰውን አደረገ። ሰው ደግሞ ባርያዎችን አደረገ። ይህ ግን፡ ከጅምሩ ጀምሮ ፍጹም ስህተት ነው። ማንም ሰው ባርያ እንዲሆን የእግዚአብሔር ሐሳብ አይደለም። አይደለም፡ የኔ ጌታ። በፍጹምም… ከዚያ በኋላ ግን የሆነውን ስሙ።

106 በዚያ ሁሉ መካከል፡ ይህ ሰው እንዲህ አለ፦ “እሺ፡ ጥቂቶቹን እኔ መግዛት እፈልጋለሁ አለ… ” ከመካከላቸው አንድን ወጣት አየ። በአለንጋ

አይገርፋትም። ትክክለኛ አቋም እንዳለው ወንዳወንድ አገጩን ሰበቅ አድርጓል፡ ራሱን ቀና በማድረግ፡ ይንጎራደዳል። ደላላውም እሱን አይቶት "እሱን መግዛት እፈልጋለሁ፡" አለ።

107 "አይ እሱ አይሸጥም፡" ብሎ መለሰለት።

108 እሱም፦ "እንዴ፡ ለምን? " አለው፡ "እሱ አለቃቸው ነው'ዴ? "

109 "አረ አይደለም፡ ባርያ ነው፡" አለው።

110 "እንዴ፡" አለው፡ "ለምንድነው? ከሌሎቹ በበለጠ ትመግበዋለህ'ዴ? "

111 "አይደለም። ባርያ ነው። ከሌሎቹ ጋር የቀረበለትን ይበላል እንጂ፡" አለው።

112 እሱም፦ "ታድያ ከሌሎቹ እጅግ የተለየ ያደረገው ነገር ምንድነው? "

113 አለቃውም እንዲህ አለ፦ "እኔንም ብዙ ጊዜ ጥያቄ ሆኖብኝ ነበር፡ አንድ ቀን ግን ደረስኩበት። በትውልድ ቦታው፡ አባቱ የጎሳው ንጉስ ነው። ምንም እንኳን ከቀዬው የራቀ መጻተኛ ቢሆንም፡ አሁንም የንጉስ ልጅ እንደሆነ ያስባል እንደ ንጉስ ልጅም ያደርገዋል።" እንግዲያውስ… ይህ አፍሪካዊ ሰው አባቱ ንጉስ እንደሆነ አስተውሎ፡ በባህር ማዶ መጻተኛ በሆነበት በማያውቀው ምድር የንጉስ ልጅ እንደሆነ ካሰበ፡ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች የሆኑ ወንዶች እና ሴቶች ምንኛ እራሳቸውን መግዛት በተገባቸው? እንደሱ ሁኑ። አዎን። ስነምግባር ይኑራችሁ፡ እራሳችሁን ግዙና እንደ እግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ኑሩ። አይገርምም፡ ምን አይነት ሁኔታ ነው።

114 ይሄው ነኝ። አቤት፡ ምስኪኗ ማርታ፡ እየሮጠች መጣችና። ክፉ ቃል ልትናገረው—የፈለገች ያስመሰልባት ነበር። "አንተ ግን እንዴት ወንድሜን አትደርስለትም? እስኪ የዋልንልህን ውለታ ተመልከት፡ አንተ ግን እኛን አዋረድከን።" መቼም፡ እንዲህ ብላው ቢሆን ኖሮ፡ የታሪኩ አጨራረስ ባለቀበት መንገድ አይሆንም ነበር። በፍጹም፡ የኔ ጌታ። የእግዚአብሔር መለኮታዊ ስጦታ አጠቃቀማችን ይወስነዋል። እግዚአብሄር ስጦታን ሲልክላችሁ፡ በአግባቡ ተጠቀሙበት። ከስጦታው አንዳች ነገር የምትጠብቁ ከሆናችሁ፡ በአግባቡ መጠቀም ይኖርባችኋል። ማርታም የሱነማይቷን እና የልጇን ታሪክ ሳታነብብ አልቀረችም መሰለኝ። ይሄን በደንብ አውቃለች። ስለዚህ እሷ… ሱነማይቷ ሴት እግዚአብሄር በኤልያስ ውስጥ መኖሩ ካወቀች፡ በኢየሱስ ውስጥስ ምንኛ አብዝቶ ይኖር ይሆን? አዎን።

115 ስለዚህ፡ አግባብ ባለው አካሄድ ሄደች። ሮጣ በእግሩ ስር ተደፋች። እንዲህ እወዳለሁ! እሱም እንዲሁ ነውና። ከእግሩ ስር ወድቃ "ጌታ ሆይ… " አለችው፡ ትክክለኛ መዓርጉም ይህ ነው። ጌታዋ ሰለ ነበር። "ጌታ ሆይ፡ አንተ በዚህ ብትኖር ኖሮ፡ ወንድሜ ባልሞተም ነበር።"

116 ኦህ፡ ማይ! ኦህ፡ ይህችን መልከ መልካም ሴት እንባ በጉንጮቿ ሲፈስ ሲያያት፡ ታላቅ ልቡ እንዴት እንደሆነ እገምታለሁ። "ጌታ ሆይ፡ አንተ በዚህ ብትኖር ኖሮ፡ ወንድሜ ባልሞተም ነበር፡" አለችው። የተናገረችውን አስተውሉ። "ጌታ ሆይ፡ አሁንም፡ ቢሞትም እንኳ፡ የቆዳ ትሎች ሰውነቱ ቢወርቱም፡ ጌታ ሆይ፡ አሁንም፡ ከእግዚአብሄር የምትለምነው ሁሉ፡ እግዚአብሄር ይሰጥሃል።"

117 ኦህ፡ ምስጢሯ ይህች ናት። “ሆስፒታሎቹን ሁሉ ዞርኩኝ። ዶክተሮች ሁሉ ትሞቺአለሽ ብለውኛል፣ አሁንም ግን፡ ጌታ ሆይ... መንቀሳቀስ አልችልም፡ በአርቲራይተስ ተሰባብሬአለሁ፡ ጌታ ሆይ፡ አሁንም ግን... ”

118 ትናንት **በህጻኑ** ራስ ወተር ሄድ ነበረ። ከአቅም በላይ ነው ምንም ማድረግ አይቻልም ነበር። ተሰፋፍቶት ትንሿ ጭንቅላቱን ከፍቶ ሊገድለው ይችል ነበር፡ “አሁንም ግን፡ ጌታ... ” አሁንም ያው አምላክ ነው። አሁንም ያው ጌታ ነው። “አሁንም፡ ጌታ... ” ሁሉን በሚችል በአምላክ ቀኝ፡ እርሱ ሰርቶልናል ስለምንላቸው ነገሮች ሊያማልድ ተቀምጦ ይገኛል።

119 አሁን፡ በእውነት። እውነተኛ መንፈሳዊነት ተሰማኝ። በማንኛውም መንገድ ሆሊ ሮለር ነው ማለታችሁ መች ይቀራል፡ ስለዚህ እናንተም ጀምሩት፡ እና ፈጽሙት።

120 ስለዚህ፡ አዎን፡ ወዳጄ፡ “አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ ከእግዚአብሄር የምትጠይቀው ሁሉ፡ እግዚአብሄር ይሰጥሃል።”

121 “የሚያስፈልጋችሁ ሁሉ አብን በሰሜ ጠይቁት፡ እኔ አደርገዋለሁ፡” ብሏል ኢየሱስ።

122 “አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ የምትጠይቀው ሁሉ፡ እግዚአብሄር ይሰጥሃል።” ኦህ፡ ይሄ ወደ ልቡ ጥልቀት ሳይደርስለት አይቀርምና።

123 “ወንድምሽ እንደገና በሕይወት ይኖራል፡” አላት።

124 እሷም እንዲህ አለችው፡- “አዎን፡ ጌታ ሆይ። መልካም ልጅ ነበር። በሕይወት ይኖራል። ሁሉ በሚነሳበት ትንሳኤ በመጨረሻው ቀን ይነሣል።” አይሁዶች በጠቅላይ ትንሳኤ ያምኑ ነበርና። “በዘመን ፍጻሜ በትንሳኤ ይነሣል።”

125 እዩት። ትንሿ ሰውነቱን ሰብሰብ አደረገና። “ትንሣኤ እና ህይወት እኔ ነኝ፡” አላት። ኦህ፡ ማይ። ማንም ሰው እንዲህ ተናግሮ አያውቅም። ወደፊትም እንዲህ ሊል የሚቻለው ሰው፡ አይኖርም። ይሄን መናገር የሚችል ብቸኛው እሱ ነው። “ትንሣኤ እና ህይወት እኔ ነኝ፡” አለ ጌታ። “በእኔ የሚያምን፡ ቢሞት እንኳ፡ ህያው ይሆናል። ህያው የሆነም የሚያምንብኝ አይሞትም። ይሄን ታምኛለሽን? ”

126 ኦህ፡ አንድ ነገር ሊሆን እንዳለ አስተውላለች። መሆንም አለበትና። “አምናለሁ፡ ጌታ ሆይ፡” አለች።

127 ከቅን ልብ የመነጨ እምነት እግዚኤብሔር ዘንድ ሲደርስ፡ የመንኰራኲር ጥርሶች **እንደዚህ** እንደመገናኘት ነው። የሆነ ነገር ይፈጠራል። ዛሬ ምሽት ከዚህ ጉባኤ ጋር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም እወራረዳለሁ፡ ልክ እንደዚሁ የእናንተም እምነት ከእግዚአብሄር ጋር ቢነካካ፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ሌላ በዓለ ሐምሳ ይኖረናል። በከተማይቱ ውስጥ የአገሪቱ ፖሊስ ሁሉ ተሰብስቦ፡ ሊቆጣጠረው የማይችል ሪቫይቫል ይቀጣጠላል። እውነት ነው። ትክክለኛ ሪቫይቫል ይኖራል። “አሁንም፡ ጌታ ሆይ... ”

128 “ጌታ፡ እኛ’ኮ፡ በዚህ **ይሄን** ጨርሰናል፤ እኛ **ይህን** አድርገናል፡ እና **ያንን** አደረግን።” አንተ ሰላደረግከው ነገር ግድ የለኻም፡ “አሁንም፡ ጌታ ሆይ... ” እያልክ እሱን እንድትጠራው እየጠበቀህ ነው። እሱ... “ይህን ታምኛለሽን? ”

በእርግጠኝነት። አዎን፡ ጌታዬ። “እሁንም ቢሆን፡ አንተ ከእሱ የምትጠይቀው ሁሉ… ”

129 “ወዴት አኖራችሁት? ” ወድያውም፡ ወደ መቃብሩ መጣ። ሰው እንደመሆኑ አለቀሰ፡ እግዚአብሄር እንደመሆኑም ሙታን አስነሳ።

130 አንድ ቀን፡ ሌሎች ቡድኖች ጋር ህብረት የምታደርግ ሴት ነበረች… ስለ ሐይማኖት ተቋማት መናገር እንደ ሱስ ሆኖብኝ አያውቅም። ሴቲቱም… ኢየሱስ ተራ ነብዩ ነው ብለው የሚያስቡ ናቸው። መለኮታዊ እንደሆነ አያምኑም። አሁን፡ እሱ… ነብዩ ብቻ ከነበረ’ማ፡ እኛ ሁላችንም ሐጥያተኞች ነን። እሱ እራሱ ከእግዚአብሔር በምንም የማይተናነስ፡ እግዚአብሔር ካልነበረ፡ ዓለም ካስተናገደቻቸው አታላዮች ቁጥር አንድ አታላይ ነው። በትክክል። እሱ ግን ከሰው በላይ ነበር። እና “መለኮት አልነበረም፡” አለች።

131 ዛሬ ዛሬ ማሕበረሰባዊው ወንጌል ውስጥ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነብዩ የማድረግ ዘመቻ ይታያል። ለምን፡ እሱ’ኮ የነብያት ሁሉ አምላክ ነው። አዎን ነው።

132 እና እሷ “‘ሰው ብቻ እንደነበረ፡’ በገዛ መጽሐፍ ቅዱስህ አረጋግጥልሃለሁ፡” አለችኝ።

133 “እስኪ አረጋግጪልኝ፡” አልኳት።

134 እንዲህ አለች፡ “ወደ አልዓዛር መቃብር በሄደ ጊዜ፡ መጽሀፍ ቅዱስ፡ ‘አለቀሰ’ ይላል። ሟች ባይሆን ኖሮ ባላለቀሰ ነበር።”

135 “እመቤት፡ ያለሽ ይሄን ቃል ብቻ ነው? ” አልኳት፡ ክፉ ቃልን ለማውጣት በመፈለግ አይደለም፡ ይሁን እንጂ ያልኳት ነገር ልንገራችሁ።

136 እሷም “ያለኝ ይሄ ነው፡” አለች።

137 እኔም “አሳብሽ እስከ ሞት ድረስ በተራበች በደሮ ጥላ ከተሰራ መረቅ ይልቅ የከሳ ነው፡” አልኳት። “እንደው፡ አንዳች የሚጸና መሰረት—የለሽም፡” አልኳት።

138 “ምን ለማለት ፈልገህ ነው፡ አለቀሰ’ኮ። ይህም ሟች መሆኑ ያሳያል፡” አለች።

139 እኔም “የሚሞት እና የማይሞት ነበር። በስጋ የተገለጠ አምላክ ነበር።” አልኳት።

140 “እይይ፡ ትርጉም አልባ!” አለች፡

141 እኔም፦ “ወደ መቃብር እያለቀሰ ሄደ። ይህ እውነት ነው፡ ትንሿ ሰውነቱ ቀና ቀና ባደረገ ጊዜ ግን… ” መጽሐፍ ቅዱስ “ደም ግባት የለውም፡ የሚማርክ ውበት አልነበረውም፡” ይላል። ነገር ግን ትንንሽ ትከሻዎቹን ቀና አድርጎ፡ “አልዓዛር ሆይ፡ ወደ ውጭ ና” ባለው ጊዜ፡ ለአራት ቀን ያህል በመቃብር በሰብሶ የሞተ ወጣት፡ ከመቃብር ወጣ። ይሄኛው ከሰው በላይ ነው። ይሄን ማድረግ የሚችል ሰው አሳዩኝ። ምንድን ነበር? መበስበስም ጌታውን አወቀ። ህይወትም ፈጣሪዋን ለየች። አንዳች ነገር መሆን ነበረበት። እሱ ስለተናገረ በመቃብር ውስጥ አራት ቀን የቆየ ሙት ሰው፡ ዳግም ተነሣ፡ በእግሮቹም ቆመ፡ ህያውም ሆነ። ሃሌሉያ! እግዚአብሔር እራሱ በልጁ በኩል ነበር። አዎን፡ የኔ

ጌታ። እግዚአብሔር እራሱን፡ በልጁ በኩል ይተርክ ነበር። የተናገረው ሰው ሳይሆን፡ እግዚአብሔር እራሱ ነበር።

142 ያኔ አንዳች የሚበላ ፈልጎ ዛፏን በተመለካት ጊዜ ሰው ነው። ያ ሰው ነበር። አምስት እንጀራ እና ሁለት ዓሳ ባርኮ፡ አምስት ሺ ባበላ ጊዜ ግን ከሰው በላይ ነው። ያበላቸው እራሱ እግዚአብሄር ነው። ከነብዪ የሚበልጥ፡ ከሰውም የሚበልጥ፡ ሰው-የሆነ አምላክ ነው። በትክክል።

143 በዚያን ሌሊት በታንኳይቱ ውስጥ በተኛ ጊዜ፡ ባሕሩም እንደ ጠርሙዝ መዝጊያ በታላቁ ባሕር መካከል እያጓራ እና እየተመመ፡ አስር ሺ የጥልቁ አጋንንት እናስጥመዋለን ብለው በተማማሉበት በዚያች ሌሊት። ለህመምተኞች ሲጸልይ ውሎ ደክሞት፡ ንፋሱ እንኳን ሳይረብሸው፡ ከኋላ በተኛ ጊዜ፡ ሰው ነበር። በተኛ ግዜ ሰው ነው፡ እግሮቹን በታንኳይቱ ጠርዝ ላይ አድርጎ፡ በተነሣ ጊዜ ግን፡ ወደ ሰማይ አየና፡ “ጸጥ በል፡ ሰላም ሁን፡” አለ፡ ንፋሳቱን እና ማዕበል ሁሉ ታዘዙለት፡ ይሄ ግን ከሰውም የሚበልጥ ነው። እግዚአብሔር እራሱን በሰው ውስጥ፡ እየተረከ ነበር። በትክክል።

144 በመስቀል ላይ ማረኝ ብሎ ባለቀሰ ጊዜ ሰው ነበር። “ጠማኝ፡” ባለ ጊዜ፡ ሰው ነበር። በሞተም ጊዜ፡ ሰው ነበር፡ በትንሳኤው ማለዳ የሞት፣ የሲኦል እና የመቃብር እስራት በጣጥሶ፡ በተነሣ ጊዜ ግን፡ ከሰው የሚበልጥ ነው፤ በስጋ የተገለጠ አምላክ ነው። ገጣሚ እንዲህ መግጠሙ አያስደንቅም፦

> እየኖረ፡ ወዶኛል፡ እየሞተም፡ አድኖኛል
> ተቀብሮ፡ ሐጢአቴን አራቀ፤
> ተነስቶም፡ ለዘለአለም አጸደቀኝ፤
> አንድ ቀን ይመጣል—አቤት፡ ድንቅ ቀን ይሆናል!

145 እንዲህ አለ፦ “እኔ ህያው ነኝና፡ ህያዋን ናችሁ። ይሄን ታምናላችሁን? ” አሁንም ትናንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው ነው። ይሄን ታምናላችሁን? መንፈስ ቅዱስ አሁን እዚህ እንዳለ አምናለሁ። ይሄን ታምናላችሁን? በመገኘቱ እንደሚሞላን አምናለሁ። ሄን ታምናላችሁን? መንፈስ ቅዱስ ህልውናውን ሁሉ አፍስሶ፡ ህመምተኞችን መፈወስ እንደፈለገ፡ መንፈስ ቅዱስ ያልተሞሉ ሰዎችን ሁሉ መሙላት እንደፈለገ አምናለሁ። ይሄን ታምናላችሁን? ከልባችሁ ታምናላችሁን? በእግሮቻችን ቆመን እናመሰግነው። አሁን በላያችን ላይ እንደሚፈስ አምናለሁ።

146 ጌታ አምላክ ሆይ፡ የሰማይ እና የምድር ፈጣሪ፡ የዘለአለም ህይወት ደራሲ፡ የመልካም ስጦታዎች ሁሉ ሰጪ፡ ጌታ ሆይ፡ እኛ “ይሄን እናምናለን።” በጉባኤው ውስጥ ያለኸው አንተ እንደሆንክ አምነናል። ነፍሳችንን የምትባርክ አንተ እንደሆንክ እናምናለን። መንፈስህን በእኛ ላይ የምታፈስሰው አንተ እንደሆንክ እናምናለን። ትናንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ አንተ ያው እንደሆንክ እናምናለን። አንተ ለዘለአለም ህያው ሆነ እንደምትኖር ሰሞቻችንም በበጉ የሕይወት መጽሀፍ እንደተጻፈ እናምናለን። ሰማይ እና ምድር ሁሉ ያልፋሉ፡ እኛ ግን በአንተ ህያውነት፡ ለዘለአለም እንኖራለን። ጌታ ሆይ፡ ቃል ገብተህልናልና። በሙሉ ልባችን አምነናል። ጌታ ሆይ፡ በእኛ ውስጥ ያኖርከው ሁሉ፡ እናምናለን። እኔ እወደዋለሁ፣ እወደዋለሁ።

147 ትወዱታላችሁን? መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ አምናለሁ። በሰውነታችን ላይ የሚፈስ ነገር ይሰማኛል። ይሄን ታምናላችሁን? ሰውን ሁሉ መፈወስ እንደፈለገ አምናለሁ። ይሄን ታምናላችሁን? እጆቻችሁን ወደ ላይ ይነሱ። በእግሮቻችሁ ቁሙ። መንፈስ ቅዱስ እዚህ አለ። ይሄን ታምናላችሁን? ጴጥሮስ ሲናገር፡ ይሄ ነው! "ይሄ ነው፡" ብሏል። መንፈስ ቅዱስ፡ ይሄው ነው።

148 የሰማይ እና የምድር ፈጣሪ፡ ጌታ ሆይ፡ ሀይልህን፣ እና በረከትህን፣ እና በጎነትህን፡ ለህዝብህ ላከው፡ ልቦቻቸውን ባርከህ፡ የሰው ልጅ ለዘለአለም ህያው እንደሆነ አሳያቸው። አድርግልን፡ ጌታ ሆይ። በእግዚአብሄር ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እነዚህን ሁሉ በፊትህ አቀረብናቸው።

149 መንፈስ ቅዱስ ያልተሞላችሁ ሁላችሁ፡ እጆችሁን ወደ ላይ አንሱና አምልኩት። በእናንተ ላይ ይፈሳል። እጆቻችሁ ጫኑባቸው። ግዜው አሁን ነው። ለምን ሌላ ግዜ እንጠብቃለን? ጊዜ አሁን ነው። የጴንጤ ቆስጤ ዘመን፡ ወደ እግዚአብሔር መመለሻ ጊዜ አሁን ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ፡ ጴንጤ ቆስጤ! የህያው አምላክ ሃይል ልባችሁን ይቀሰቅሰው። ነፍሳችሁ የሚያጠራ፡ የእሱ መንፈስ ወደ እናንተ ይቅረብ። ህመምተኞችን ለማዳን፡ ዕውሮችን ለማብራት፡ ከማታ እስከ ማታ ድረስ አለ፡ በታላቁ እና በከበረው ኃያልነቱ ዘወትር ያው እንደሆነ ለማሳየት ህያው ነው። ሃሌሉያ!

150 አመስግኑት። እጆች ይነሱ። ያላችሁበትን እርሱ፡ በመገኘቱ እና በበጎነቱ እንዳላችሁ፣ በክብሩ፣ እና በስልጣኑ፣ ለዘለአለም በጸናው ምሕረቱ፣ እንዳላችሁ ብቻ እወቁ። ለዘለአለም አይቀያየርም። የጌታ ስም የተባረከ ይሁን። ሃሌሉያ! ኦህ፡ ቅዱስ ሰሙን ባርኩ።

151 አቤት፡ እንዴት ድንቅ ነው፡ እንዴትስ ኃያል ነው። እስኪ ሰንቶቻችሁ፡ ህይወታችሁን ለእግዚአብሔር ማስገዛት ትፈልጋላችሁ? እጆቻችሁ ይነሱ። ስንቶቻችሁ ህይወታችሁን ለእግዚአብሔር ማስገዛት ትፈልጋላችሁ? ይሄው ነው። እጆቻችሁ ይነሱ። ጴንጤ ቆስጤን እንየው። የእግዚአብሔርን ህዝብ እንያቸው። እኔም እጆቼን አነሣለሁ። "ጌታ ሆይ፡ እነሆኝ። እኔን ላከኝ።" ጌታ ሆይ፡ የመስውያው ፍም በመልአኩ ውሰድና ኃይልህን በእኛ ላይ ላከው። እግዚአብሔር፡ አባት ሆይ፡ መንፈስህን በሙላት ስጠን። ጌታ ሆይ፡ ጸሎታችንን ሰማ። በእምነት እንደጸኑ ልጆችህ፡ ጸሎታችንን ሰማ። ክብር ለስሙ ይሁን።

152 ኦህ፡ እንደሚተምም የክብር ማዕበል፣ ኦህ፡ እንደ ምሕረትህ የጤዛ ጠብታ። ኦህ፡ ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን። ነፍሳችን ትጠብቅህ። ይሄን ታምናላችሁን? ይሄን ታምናላችሁን? የሚመጣው መንፈስ ቅዱስ ይሄ ነው። ወደ ጴንጤ ቆስጤው በረከት፡ ወደ እግዚአብሔር መንግስት የሚነዳን የማይታየው ኃይል ይህ ነው። ወደ ቤቱ ተመለሱ። ወደ ቤት ትፈለጋላችሁ። ድንቅ ህዝብ ናችሁና። እግዚአብሔር ህይወታችሁን እንድታስገዙለት ይፈልጋችኋል። ሴቶች ሆይ፡ እራሳችሁን አንጹ። ወንዶች ሆይ፡ እራሳችሁን ቀድሱ። በእውነተኛ እና በንጹሕ ልብ ወደ እግዚአብሄር እንመለስ እና እግዚአብሄርን እናገልግለው።

153 እግዚአብሔር ይባረክ፡ መንፈስ ቅዱስ በጉባኤው ሰፍረዋል። እንደመራችሁ ሁኑ። መንፈስ ቅዱስ እንዲሰራባችሁ ፍቀዱለት። ሌላ የምለው የለኝም። አሁን ምን ኣንደምልም አላውቅም። መንፈስ ቅዱስ በህንጻው ሁሉ ሞልቷል። የጌታ ስም ይባረክ። ኦህ፡ ሃሌሉያ! ሃሌሉያ! ክብር ለጌታ ይሁን።

ክብር ለጌታ ይሁን። ጌታ ይባረክ። እንዴት ድንቅ፡ እንዴትስ ክቡር ነው… የአምላክ ቅዱሳን ምስጋና በፊቶቻችሁ፡ እንዴት ውብ እንዴትስ ድንቅ ነው፡ እየተመላለሰ ክብሩን በሚያሳየን በመንፈስ ቅዱስ መገኘት ከዚህ ከታላቅ ጉባኤ ስሙን ለማወደስ፡ በአንድነት የሚሰማ።

154 ወደ ቀኛችሁ ዞራችሁ አጠገባችሁ ካለው ሰው ጋር ሰላምታ ተለዋወጡ፡ “ጌታ ይባረክ፡ ወንድሜ። ጌታ ይባረክ፡ እህቴ፡” ተባባሉ። እንስተካከልና እግዚአብሄር ይቀሰቅሰን። ጌታ ይባረክ። ትክክል። ሜተዲስቶች፣ ባፕቲስቶች፣ እና ፕረስቢተርያኖች፣ ጴንጤ ቆሰጤዎች፣ ሰሸንዝ ደይ አድቬንቲስቶች፣ ሌሎቻችሁም፡ በጌታ በእግዚአብሔር ህልውና ፊት ተጨባበጡ። እንዲህ ነው። ኦህ፡ ሃሌሉያ! ሃሌሉያ! ሃሌሉያ! ኦህ፡ እኔም አንዱ ነኝና ደስተኛ ነኝ። ደስተኛ ነኝ። ኦህ፡ ዝገትን የሚያስለቅቁ እንባዎች በግድግዳዎቹ ላይ ይውረዱ። ክብር! ቅዱስ ስሙ ይባረክ፡ የጌታ ነጻነት ይሁን… የጌታ ስም ብሩክ ይሁን። ኦህ፡ ሃሌሉያ! እግዚአብሔር ይባረክ።

155 ኦህ፡ ሰዎች ፊቶቻቸውን አብርተው፡ እጅ ሲጨባበጡ ማየት ደስ ይለኛል። የእግዚአብሔር ኃይልም፡- “እንዲህ ነው። እንዲህ ነው፡ የእግዚአብሄር ልጆች ነንና ይላል። እኛ በክርስቶስ ዘንድ፡ አንድ ትልቅ አካል ነን፣ ሙሽራው ነን፣ ታላቂቱ ነን።” የጌታ ምጽአት ቀርቧል። ህዝቡም በፍቅር እና በህልውናው ኃይል… አንድ ሆነው ተዋደዋል። ኦህ፡ ይህ እንደ ገነት ነው። ኦህ፡ ደስ ይላል። አሜን። አቤት፡ እንዴት ውብ፡ እንዴትስ ድንቅ ነው፤ ጌታ በመንፈስ እና በኃይል ማምለክ መቻላችን ድንቅ ነው። (ለመፈጸም፡ የጀመርነው።) ልዩ ጊዜ ነው።

156 ወንድሞችን… አረ እንደው አይሆንም አልኳቸው፡ “ወንድሞች ሆይ፡ ማቆሚያ ሰፍራ የለውም።” እዚህ ሰፍራ የለም… አልጀመርነውምና፡ እናቆመውም። በቃ—በቃ ልዩ ነው… ሰንቶቻችሁ ደስ ብሏችኋል? በቃ የጌታ መገኘት፡ ኦህ፡ ማይ፡ ልዩ ነው፡ የጌታ መገኘት በዚህ አለ።

157 እመኑት ብቻ። የእግዚአብሄር መገኘት፡ ህመምተኞችን ለመፈወስ፡ ሰዎቹን ጤነኛ ለማድረግ በዚህ አለ። ታምኑታላችሁን? ካመንነው፡ የማይቻል ነገር የለም። ታምናላችሁ? ይሄ የጌታ መገኘት እንደሆነ ታምናላችሁ?

158 አሁን፡ ባላችሁበት… ትንሽ ጊዜ ሰጡኝ፡ አሁን ትንሽ ጊዜ ብቻ፡ ለአፍታ ብቻ አድምጡኝ። መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ላረጋግጥላችሁ። እነኚህን ነግሮች የተናገራችሁ፣ እና ያደረገ መንፈስ ቅዱስ፡ ይሄን እንደሚያውቀው ላሳያችሁ። እስኪ ወደዚህ ሰፍራ ታማችሁ የመጣችሁ ሰንቶች ናችሁ? እጆቻችሁን አሳዩን። ህመምተኞች የሆናችሁ ብቻ… ያውና ሰዎች…

159 እዚያ ጋር አንድ ሰው ቆሟል። ታምናለህ፡ ጋሼ? የጸሎት ካርዶች የለም፣ ግን እግዚአብሔር ሊፈውስህ እንደሚችል ታምናለህ? ችግርህን ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ? ችግርህ ጎንህ ጋር ነው። ቀዶ ጥገና ለመደረግ ቀጠሮ ይዘሀል። ትክክለኛ ነው። ሰምህ አቶ/ ካርትራይት ትባላለህ። ትክክል ነው። ልክ ነው? እጅህን አወዛውዝ። በጣም ጥሩ። አንተ አትፈልገውም፡ ወደ ቤትህ ሂድና ተፈወስ። ታምናለህ?

160 ህጻን ልጅ ክንድህ ላይ ያቀፍከው ሰውየ፡ እኔ የእግዚአብሔር ባርያ እንደሆንኩ ታምናለህ? ይህስ ከመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ታምናለህን? እኔ አንተን አላውቅህም፡ ልክ ነው? በዘመኔ አይቼህ አላውቅም፡ እንግዳ ነን።

የህጻኗ ችግር መንፈስ ቅዱስ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ? ሽፍታ አለባት። ትክክል። አይደለም'ዴ? በርግጠኛነት። ከዚህ አገር አይደለህም። አይደለህም። አንተ እራስህ፡ በጣም የምትሰቃይበት፡ የሆድ ህመም አለብህ። ትክክል፡ አይደለም'ዴ? ከካንሳስ ከተማ ነህ። በጣም ጥሩ። ኢየሱስ ክርስቶስ ፈውሶሃልና፡ በደህና ተመለስ። ሃሌሉያ! አምነሃል። በሙሉ ልብህ አምነኸዋል?

161 የእግዚአብሄር መል እክ በላይዋ ላይ የሚያንዣብብባት—ምስኪን ሴት፡ አሮጉት እዚያ ጋር አለች፡ በሄርኒያ የምትሰቃይ ናት፡ እዚያ ጋር ተቀምጣለች። እህቴ፡ እግዚአብሄር ከሄርኒያ እንደሚፈውስሽ ታምኛለሽ? አንቺ፡ ትንሽ ቀይ አበባ ያላት ኮፍያ ያጠለቅሺው፡ እጆችሽን ከፍ አድርጊ። በጣም ጥሩ። ተፈውሰሽ ወደ ቤትሽ ሂጂ። አሜን። እግዚአብሔር ነው፤ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነው። ከሙታን ተነስቷል። ዛሬ በዚህ አለ።

162 አሁን፡ እርስ በርሳችሁ እጆቻችሁን ጫኑ እና መልካም ጊዜ እንዲሆንላችሁ ጸልዩ፡ ሁላችሁም፡ እኔም አንድ ሰው እጠራለሁ። ወደዚህ ና፡ ወንድሜ። እግዚአብሔር እንደፈወሳችሁ ለማሳየት እርስ በርሳችሁ እጃችሁን ስትጭኑ፣ ለእኔ ደግሞ ጸሎት የሚያቀርብ ወንድም እዚህ አለኝ። (በጣም ጥሩ። አሁን ቀጥሉ።) ጌታ እግዚአብሔር ይመስገን።

**ይህን ታምኛለሽን?** AMH60-0402

(Believest Thou This? )

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በእንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ቅዳሜ ቀን፣ ሚያዝያ 2፣ 1960 በዩ/ኤሰ/ኤ ኦክላሆማ፣ በቱልሳ፣ በሚገኘው የማዘጋጃ ቤት አዳራሽ፣ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2022 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org